# መጽሐፍ ቅዱስን
## የማስተማር ዘዴ

ለአዲስ መምህራን ማሠልጠኛ
የተዘጋጀ መምሪያ

# መግቢያ

በአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ውስጥ የተፈጸሙ ታሪኮችን የሚናገረው፥ በአርባ የተለያዩ ሰዎች የተጻፈው፥ ስልሳ ስድስት መጻሕፍትን የያዘውና እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ያለውን ፈቃድ የሚገልጸው መጽሐፍ ቅዱስ በዘመናችን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች፡- "ሕይወት ምንድን ነው? ትክክለኛው መንገድ የቱ ነው? እውነት ማለት ምን ማለት ነው?" ብለው ለሚጠይቁአቸው ጥያቄዎች "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ..." የሚለውን አምላካዊ መልስ የሚሰጥና በዚህ ዓለም ላይ ለምን እንደምንኖር፥ እንዴት መኖር እንዳለብንና በሕይወታችንም እንዴት ደስታ ማግኘት እንደምንችል የሚነግረን ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ የተለየ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የአማኞች የዕለት መና፥ የዕለት መሪና ጽኑ መሠረት ነው። ስለዚህ በየዕለቱ መነበብና መጠናት አለበት። ለትምህርት፥ ልብን ለማቅናት፥ ለተግሣጽና ለጽድቅ መንገድ ምክር የሆነውን ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማካሄድ ያለብን እንዴት ነው? ሌሎች መጻሕፍትን በምናጠናበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱስንም እናጥና? ወይስ የተለየ ዘዴ አለው? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እና ከሌሎች መጻሕፍት ሁሉ የተለየ ስለሆነ ልዩ የአጠናን ዘዴ ሊኖረው ይገባል።

ሕግ ያመለከተውን፥ ነቢያትም የተነበዩለትን፥ በዓለም ታሪክ ከተፈጸሙ ድርጊቶች ሁሉ ብልጫ ያለውን ትምህርት የሚያሳየንን መጽሐፍ ቅዱስ ለሌሎች እንዴት ማስተማር እንደሚገባን አንዳንድ ዘዴዎችን እንድትጠቁመን ይህች አነስተኛ መጽሐፍ ተዘጋጀች። ስለዚህ የዚህ ቅዱስ ተግባር ተሳታፊ የሆነ አማኝ ሁሉ መጽሐፍዋን በጥንቃቄ፥ በጸሎትና በ- ተመስጦ ልብ እንደሚገለገልባት ተስፋ እናደርጋለን።

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በሥልጠና ላይ ለሚገኙ አዳዲስ መምህራን ነው። ይህ መጽሐፍ በአገልግሎት ላይ መዋል ያለበት በእያንዳንዱ የሥልጠና ፕሮግራም ማብቂያ የመጨረሻ ዓመት ላይ ነው። ይህ የተግባራዊ ትምህርት መምሪያ ስለሆነ ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ሁሉ ለመለማመድ መድፈር ይገባቸዋል። መጽሐፉን አንድ ጊዜ ከዳር እስከ ዳር በመዝለቅ አጥንቶ ፈተናን ማለፍ ብቻ በቂ አይደለም።

በየሳምንቱ አንድ ትምህርትን በክፍል ውስጥ የመከታተያና ሌላ ደግሞ በተግባር የመተርጎሚያ ክፍለ ጊዜ ሊኖር ይገባል። በተግባር በመተርጎሚያ ክፍለ ጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ በየተራ እየተነሣ በሌሎቹ ተማሪዎች ፊት ቆሞ ምን እንደተማረ መናገር አለበት።

ስለ መጽሐፉ መሻሻል የምታቀርቡት አስተያየት ካላችሁ፤

የመ. ሣ.ቁ. 127

አዲስ አበባ

ብላችሁ በጽሑፍ ላኩልን።

# ክፍል አንድ

## ትምህርት አንድ

## ታላቁ መምህር ኢየሱስ

ኢየሱስ ክርስቶስ ከታወቁት መምህራን ሁሉ ታላቅ ነበር። ታላቅ መምህር ያደረገው ምን ነበር? ሌሎችን ያስተማረውስ እንዴት ነበር? ይህ ክፍል ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች አንዳንድ መልሶችን የመጠቆም ሙከራ ያደርጋል።

## ፍሬ አሳቦች

ሀ. 1. ኢየሱስ ያስተማረው የትምህርት ማዕከል በሆኑት ምኵራቦች ውስጥ ነበር። ከእግዚአብሔር የሆነውን ያስተምርና እንደሚያስተምረውም ቃል ይኖር ስለነበር ሕዝቡ ሁሉ "ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው..." በማለት ይገረሙ ነበር። እኛስ? (ማቴ. 13:54፥ ዮሐ. 6:59 ና ሕዝ. 7:10)።

2. ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትተውና ንቀው ሕዝቡ በሰብዓዊ ሕግና ሥርዓት እንዲኖር በማስገደዳቸው "ወጋችሁን እንድትጠብቁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል" በማለት ፈሪሳውያንን ገሰጻቸው (ማር. 7:9)። ሲያስተምርም "በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ" በማለት ሕዝቡ እርሱን እንዲመስልም ለመንገር አምላክህንና ጎረቤትህንም ውደድ በማለት ትእዛዝን ሰጥቶአል (ሉቃ. 9:23)።

3. ኢየሱስ "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ..." "ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል"

"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ" "እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ" በማለት ተከታዮቹ ሁሉ እምነታቸውን ተግባራዊ በማድረግ ለሌሎች ምሳሌ እንዲሆኑ አስተምሯል (ማቴ. 7:20፤24፤ ዮሐ. 14:15፥ 15:14)።

4. የሐዋርያት ሥራ ስለተለወጡ ሕይወቶች ደጋግሞ ይናገራል። እነዚህ የተለወጠ ሕይወትን ያገኙ ሰዎች ይህንን ሕይወትን የሚለውጠውን መልእክት ለሌሎች ማስተላለፍ ነበረባቸው። ከእግዚአብሔር የሆነ ሃይማኖት እውነተኛ ውስጣዊ ልምምድ በመሆኑ ሊጠፋ ወይም ሊደክም አይችልም (የሐዋ. 5:38-39)።

ለ. ለማስተማር ስድስት ዋና ዋና ነገሮች ያስፈልጋሉ።

1. መምህር
2. ተማሪ
3. ቦታ
4. የሥርዓተ ትምህርት መምሪያ
5. ዓላማ
6. የማስተማር ዘዴ

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ያስተማረውን በመመልከት ከዚህ

በላይ ከተጠቀሱት ስድስት ነገሮች ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ እናስተውል፡፡

1. መምህሩ- ኢየሱስ
2. ተማሪው /ዋ/ -ሰማርያዊቷ ሴት
3. ቦታው - የያዕቆብ ጉድጓድ
4. ትምህርቱ - የሕይወት ውኃ
5. ዓላማው - የሕይወት መለወጥ
6. የማስተማር ዘዴው - ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፡፡

ሀ/ ምንም እንኳ ያገኛት ብዙ ከመሄድ የተነሣ ደክሞት ሲያርፍ ሳለ ቢሆንም የተሰጠውን ዕድል ተጠቀመበት እንጂ ሴቲቱን ዝም ብሎ ሊያልፋት አልፈለገም (ዮሐ. 4፡6-7)፡፡

ለ/ አሳብዋን ለመሳብ በመጀመሪያ "ውኃ አጠጪኝ" በማለት ተናገራት (ዮሐ. 4፡7)፡፡

ሐ/ ይህም እነጋገሩ ስላስደነቃት እርሱ የሚነግራትን የመስማት ፍላጎት አደረባት (ዮሐ. 4፡9)፡፡

መ/ የውይይት ዘዴንም ተጠቀመ፡፡፡

ሠ/ ይህችን ሴት በግል በማነጋገሩ ብዙ ሌሎች ሰዎችን ለማግኘትና ለማሳመን መልካም በርን ከፈተለት (ዮሐ. 4፡39-42)፡፡

ረ/ ትምህርቱን ሴቲቱ ለምትጠይቃቸው ጥያቄዎች በሚሰጣቸው መልሶች አስታክኮ ይገነባ ነበር (ዮሐ. 4፡9-10ና 4፡11-15)፡፡

ሰ/ ኢየሱስ ሴትዮዋ የነበረባትን ችግር በማወቁ ሕሊናዋን የሚነካ ንግግር መጠቀም ፈለገ፡፡ እርሷ ግን ከዚህ እውነት ራስዋን ለመደበቅ ፈለገች፡፡ ነገር ግን በነገሩ ላይ የተሰነዘሩት የኢየሱስ መልሶች እርሷን ወደ ዋናው ቁም ነገር ሊያመጡአት ወይም ሊመልሷት ችለዋል (ዮሐ. 4፡16)፡፡

ሸ/ ልታደርግ የሚገባትን ነገራት (ዮሐ. 4፡16)፡፡

ቀ/ ሰው ምን ይለኛል በማለት እራሱን አላስጨነቀም፡፡

በ/ እርሱ ተማሪውን በሚገባ ያውቃል፥ በሕይወትዋም ያለባትን ችግር ያውቃል (ዮሐ. 4፡17-18)፡፡

ሐ. 1ኛ ቆሮ. 3፡9 እኛ ሁላችን ከእግዚአብሔር ጋር ሠራተኞች እንደሆንን ያስተምረናል፡፡ ስለዚህ የሰዎችን አስተሳሰብና አቋም ማጥናት አለብን፡፡ ለመልካም ውጤት እንዴት እንደሚማሩና ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት እንደሚሠሩ ማወቅ ያስፈልገናል፡፡ አንድ ገበሬ ዘሩን ከመዝራቱ በፊት እርሻውን ማዘጋጀትና ማለስለስ አለበት፡፡ ከዚያም ዘሩን በጥንቃቄ በመዝራት አረሙን በወቅቱ እያረመ በመቆጣጠር አጥጋቢ ምርትን ለማግኘት ተስፋ ይኖረዋል፡፡ እኛም የጌታን ቃል የምንዘራ ሁሉ በተቻለን አቅም ማስተማርና ማዘጋጀት አለብን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ራሱ ለእኛም ሆነ ለምናስተምራቸው ሰዎች ታላቁ አስተማሪና መሪ መሆኑን መዘንጋት የለብንም (ዮሐ. 14፡26፥ 16፡8-13)፡፡

ተማሪዎቻችን እውነተኛ ልባዊ ለውጥ አግኝተው "ያንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን" በሚሉበት ጊዜ ይህ የማስተማራችን እውነተኛ ውጤት ይሆናል፡፡ ይህም እስከሚሆን ድረስ ጊዜና ከባድ መሥዋዕትነት ስለሚጠይቅ ትዕግሥት ያስፈልገናል፡፡

## ማጠቃለያ

ኤፌ. 4፡11-12ን በመመልከት ወንጌላውያን፣ መጋቢዎችና አስተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያን መሰጠታቸውን እናረጋግጣለን።

ወንጌላውያን፡- መሠረትን የሚመሠርቱ ናቸው።

መጋቢዎች፡- መንጋውን የሚያሠማሩ፥ የሚጠብቁ፥ የሚቆጣጠሩና የሚንከባከቡ ናቸው።

አስተማሪዎች፡- መንጋውን በቃሉ የሚመግቡ፥ የሚገነቡና የሚያንጹ ናቸው (ኤፌ. 4፡13-16)።

ክርስቲያኖች እስከ ክርስቶስ ሙላት ድረስ እንዲያድጉ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሰዎች በሙሉ አስፈላጊ ናቸው።

# ትምህርት ሁለት

# መምህርና ተማሪዎቹ

## መግቢያ

ነፍሳትን ለማዳን ቃሉን ከማስተማር የሚበልጥ ሌላ ዕድልና ኃላፊነት የለም። የሰውን ሥጋዊ ችግሮች ለማቃለልና በሽታዎችን ለመከላከል የሕክምና አዋቂዎች ለብዙ ዓመታት ያላሰለሰ ጥናትና ምርምር ያደርጋሉ። ስለ መንፈሳዊ ችግሮች አደራ የተሰጣቸውስ ምን ያህል ጥረት ማድረግ ይኖርባቸው ይሆን?

## ፍሬ አሳቦች

### 1. ለመምህራን አስፈላጊ የሆኑ ነጥቦች

ሀ. መምህራን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እድገት እንዲያገኙ በቂ የጸሎትና ቃሉን የማጥኛ ጊዜ ሊኖራቸው ይገባል።

ለ. የጥናት ትምህርቱንም የሚያዘጋጁበትን ጊዜ ማቀድ አለባቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለትምህርት፥ ልብን ለማቅናት፥ ለተግሣጽና ለጽድቅ መንገድ ምክር ይጠቅማል።

ሐ. መምህራን በአእምሮአቸው እንዲጐለምሱና የአስተሳሰባቸውም አድማስ እንዲሰፋ የጊዜውን ሁኔታ የሚገልጹ ጥሩ ጥሩ መጻሕፍትንም ጭምር ማንበብና አንዳንድ ጊዜም ውይይት ማድረግ አለባቸው።

መ. ለአካል ጥንካሬና ለአእምሮም ንቃት ጊዜ እንዲያገኙ በቂ እረፍት ማግኘት፥ የሰውነት ማጠንከሪያ ልምምድ መሥራትና ተመጣጣኝ ምግቦችንም መመገብ አለባቸው።

ሠ. የሰውነታቸውንም ንጽሕና በመጠበቅ ጥሩ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይገባል። በአጠቃላይ መምህራን በሕይወታቸው የሌሎች ትምህርት ቤቶች

መሆን አለባቸው።

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እንደመሆናችን መጠን የምናገለግለው ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ነውና ይህ አገልግሎት ፍጹም የሆነ ዝግጅትና የተሰጠ ሕይወትንም ጭምር ይጠይቃል። በግድ የለሽነት የተዘጋጀ ወይም ግማሽ አገልግሎት ለእግዚአብሔር ማቅረብ የለብንም። ንጹሕና ፍጹም የሆነ መሥዋዕት ማቅረብ አለብን (1ኛ ሳሙ. 24:24፥ ሚል. 1:6-9)።

3. የማስተማሪያው ክፍለ ጊዜ የተወሰነ ስለሆነ ማስተማር የሚገባውን እንደ አስፈላጊነቱ በብቃትና በጥልቀት ማስተማር እንዲችል የትምህርቱን ዕቅድ ማዘጋጀት አለበት።

መምህሩ ዕቅዱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማስተዋል ይገባዋል።

ሀ. የሚያስተምራቸው ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ - ሕፃናት ናቸው ወይስ አዋቂዎች? ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች? የተማሩ ናቸው ወይስ ያልተማሩ? አማኞች ናቸው ወይስ ያላመኑ? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ናቸው ወይስ ተራ አባሎች? ወዘተ።

ለ. ያለውን የጊዜ መጠን - በቀን ስንት ሰዓት? በሳምንት ስንት ቀናት? ወዘተ።

ሐ. ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በምን ላይ እንደሚያውሉት - በቤተ ክርስቲያን እንዲያስተምሩ? በክርስትና ሕይወታቸው እንዲያድጉ? ስለ ኢየሱስ እንዲያውቁ? ወንጌላውያን እንዲሆኑ? ወዘተ።

መምህሩ የትምህርቱን ዕቅድ አዘጋጅቷል የምንለው በእርግጥ ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎችና ለመሰሎቻቸው መልስ ሲያገኝ ብቻ ነው። ብቃት ያለው ዝግጅት ያደረገ መምህር ተማሪዎቹ ሊጠይቁአቸው የሚችሉትን ጥያቄዎች አስቀድሞ መገመት ስለሚችል ለሚጠየቁትም ጥያቄዎች በድፍረት ትክክለኛ መልሶችን መስጠት ይችላል።

4. በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩት ክርስቲያኖች የወንጌልን መልእክት በሚነግ ያስተማሩት በሕይወታቸውም ጭምር ተግባራዊ በማድረግ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራንም እውቀትና የሕይወት ልምምድ ያስፈልጋቸዋል።

5. የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ማመን አለበት፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ... ተጽፎአል እያለ መልስን ይሰጥ የነበረው በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ላይ እምነት ስለነበረው ነው። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ በሚያስተምረው ትምህርት ላይ እምነት ሊኖረው ይገባል። የምታስተምረው ለሰዎች ስትል ነው ወይስ እግዚአብሔር የሰጠህ አገልግሎት ስለሆነ?

6. አስተማሪው ተማሪዎቹን ማወቅ አለበት።

   ሀ. ከቀላል ወደ ከባድ የሚለውን የማስተማር ዘዴ በመጠቀም ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲከታተሉት መርዳት እንጂ ሊገነዘቡት የማይችሉትን ነገር አምጥቶ በመደንቀር ለትምህርቱ ያላቸውን ፍላጎት መዝጋት ተገቢ አይደለም። ለዚህም የተማሪዎቹን የእውቀት ደረጃ ጠንቅቆ ማወቅ ጠቃሚ ነው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ከብዙ ዓመታት በፊት የተጻፈና አሁን ላለንበት ዘመን ችግር፥ ተስፋ መቁረጥ፥ ወዘተ.... መፍትሔ የሚሰጥ ስለሆነ የተማሪዎቹን ችግር፥ ፍርሃት፥ ፈተና፥ ወዘተ.... ማወቅ ያስፈልጋል።

ሐ. ገና ትምህርት ሲጀምር አሳባቸውን መሰብሰብና መሳብ እንዲቻል የሚያስደስታቸውን ነገር ወይም ፍላጎታቸውን ማወቅ ያስፈልጋል።

መ. ኢየሱስ ክርስቶስ ካስተማረ በኋላ የተማሩትን በሥራ ላይ እንዲያውሉ ላካቸው። ተማሪዎቹ የተማሩትን በተግባር እንዲተረጉሙ ማደፋፈርና መርዳት ያስፈልጋል። ይኸውም እንዲያስቡ፥ ፍላጎታቸው እንዲነሣሣና በሥራ ላይ እንዲያውሉት ማለት ነው።

ሠ. ተማሪዎቹ በክርስቶስ አርአያነት በመኖር ክርስቶስን እንዲከተሉ መምራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 4፡16፥ 11፡1 እንዲሁም በፊልጵ. 3፡17 የተናገረውን ተመልከቱ።

## ማጠቃለያ

ትምህርታችን ውጤት እንዲኖረው ከተፈለገ አስተማሪዎች ከተማሪዎቻችን ጋር መግባባት አለብን። ይህም ከክፍል ውጭ መሆን ስላለበት ጊዜ ይወስዳል፤ ቢሆንም ውጤቱ ከድካሙ ይበልጣል።

# ትምህርት ሦስት

## የትምህርቱ አዘገጃጀትና ዓላማው

### መግቢያ

ክቡር እንግዳ ወደ ቤትህ ለምሳ ብትጋብዝ አስቀድመህ ምን ታደርጋለህ? የእግዚአብሔርን ቃል ለማስተማር ስናስብስ አስቀድመን ምን ማድረግ አለብን?

### ፍሬ አሳቦች

የማስተማር ዋነኛውና በጣም አስፈላጊው ክፍል ጥሩ ዝግጅት ነው። ዝግጅት ሲባል ትምህርቱን ብቻ ሳይሆን እራስንም ጭምር ያጠቃልላል። አንዳንድ አስተማሪዎች እንደሚሉት የ30 ደቂቃ ትምህርት ለመስጠት የ30 ሰዓት ዝግጅት ይጠይቃል።

ሀ. እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን?

1. የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለማግኘት መጸለይና ማሰላሰል አለብን።
2. ዓመቱ ከመጀመሩ በፊት የዓመቱን ጠቅላላ መርሃ-ግብር አዘጋጁ። ለምሳሌ:- እያንዳንዱ የትምህርት ወቅት የሚጀመርበትን፥ ትምህርት ቤት የሚዘጋበትን፥ የሕዝብ በዓላትን፥ ፈተና የሚሰጥባቸውን ቀናትና፥ ወዘተ....በትክክል ማወቅ አስፈላጊ ነው።
3. ከዚያ በኋላ:-

....በእያንዳንዱ የትምህርት ወቅት ውስጥ ስንት ሳምንታት እንዳሉ፤

... የምናስተምራቸው የትምህርት ዓይነቶችና በሳምንቱ ውስጥ ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ስንት ክፍለ ጊዜያት እንዳሉ እንረዳ። ይህ የዓመቱን አጠቃላይ መርሃ-ግብር ይሰጠናል።

4. ከዚህ በኋላ ያሉትን አስተማሪዎች መጠንና ለማስተማር የሚፈልጉትን ትምህርት ጥራት፥ የትምህርቶቹን ዓይነትና ክፍሎቹን በአእምሮአችን ይዘን የሳምንቱን መርሃ-ግብር እናወጣለን።

5. እያንዳንዱ አስተማሪ በአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ምን ያህል ማስተማር እንዳለበት ለማወቅ የአንዱን ክፍለ ጊዜ ደቂቃዎች ከሚያስተምረው ትምህርት መጽሐፍ ገጾች ወይም ምዕራፎች ጋር ማገናዘብ አለበት። እንግዲህ በዚህ መሠረት መርሃ-ግብሩ ይዘጋጃል ማለት ነው።

   ይህ መደረግ ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከመከፈቱ በፊት ነው።

ለ. አስተማሪው በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚያስተምረውን ትምህርት በጥንቃቄ ማቀድና ማዘጋጀት አለበት። ይህንንም ትምህርት ቤት ከመከፈቱ በፊት በዕረፍት ጊዜው አዘጋጅቶ ቢመጣ የተሻለ ነው። አለበለዚያ በየቀኑ ጊዜ በመውሰድ ማዘጋጀት አለበት። ትምህርቱ መቼ፥ የትና እንዴት ይዘጋጅ?

ለማዘጋጀት -1/ አመቺ ጊዜ ምረጥ፥ ማለዳ፤ ከትምህርት በኋላ፤ ወዘተ...።

2/ አመቺ ቦታ ምረጥ፥ ጸጥ ያለ ቦታ፤ ምናልባትም በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ ሊሆን ይችላል።

3/ የሚያስፈልጉህ መጻሕፍት በአንተ ዘንድ ወይም በአቅራቢያ መኖራቸውን አረጋግጥ። እነዚህም መጻሕፍት፥ መጽሐፍ ቅዱስ፥ የአስተማሪ መምሪያ፥ መዝገበ ቃላት፥ ካርታ፥ ተጨማሪ የማብራሪያ መጻሕፍትና ወዘተ ... ሲሆኑ፥ ልዩ ልዩ ዓይነት ቀለም ያላቸው ብዕሮችም ያስፈልጉህ ይሆናል። ለእያንዳንዱም የትምህርት ዓይነት የራስህ የሆነ የተለያየ ደብተር ሊኖርህ ያስፈልጋል።

4/ የምታስተምረውን ትምህርት ርእስ አጥና።

ሀ. የትምህርቱን ምንባብ ከዳር እስከ ዳር አንብበው።

ለ. ታሪኩ እንዲገባህ ደጋግመህ አንብበው። በዚህን ጊዜ የተፈጸሙ ሁኔታዎችን፥ የሰዎችንና የቦታዎችን ስሞች፥ ወዘተ... ለይተህ ጻፍ። አዳዲስ ቃላት ወይም ቦታዎች ካሉ ትኩረት አድርግባቸው።

ሐ. ለተጨማሪ ማብራሪያ ሌሎች መጻሕፍትን አገናዝብ።

5/ ስለ ተማሪዎችህ አስብ፥ የሚያስፈልጋቸውም የተለየ ነገር እንዳለ አሰላስል።

6/ ተማሪዎቹ በዕለታዊ ኑሮአቸው ትምህርቱን እንዴት ሊተረጉሙት እንደሚችሉ በማሰብ ትምህርቱን ተግባራዊ ለማድረግ ሞክር።

## ማጠቃለያ

የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን እንደ መሆናችሁ መጠን ከሌሎች አስተማሪዎች ሁሉ የበለጠ ኃላፊነት አለባችሁ፤ ስለዚህ ለዝግጅት ሰፊ ጊዜ ሊኖራችሁ ይገባል። ለጸሎትና ለዝግጅት ጊዜ ከሌለን በራሳችንም ሆነ በተማሪዎቻችን ሕይወት በረከት መጠበቅ አይገባንም።

# ትምህርት አራት

## የትምህርቱ ንዑሳን ክፍሎች

ትምህርቱ አምስት ንዑሳን ክፍሎች አሉት።

ሀ. ዓላማ:- አስተማሪው ዝግጅት በሚያደርግበት ወቅት የሚመራው በዓላማው ነው።

ለ. መግቢያ:- ይህ ደግሞ የትምህርቱ ቁልፍ ነው። በመግቢያው አማካይነት የተማሪዎቹን አሳብ መሰብሰብ ይቻላል።

ሐ. የትምህርቱ ሐተታ:- ተማሪዎቹ እንዲያውቁት የሚያስፈልገውን ቁም ነገር የሚያጠቃልል ዋናው ክፍል ነው።

መ. ምክር:- ትምህርቱን በዕለታዊ ኑሮ ውስጥ እንዴት መተረጉም እንደሚገባ የሚያስተምር ክፍል ነው።

ሠ. መደምደሚያ:- ትምህርቱን በአጭሩ የምናጠቃልልበት ክፍል ነው።

## የትምህርቱ ዓላማ ጥቅምና አዘገጃጀት

በመጀመሪያ ዓላማ ምን እንደሆነ እንመለከታለን። ለሕይወትህ ዓላማ አለህ? ሐዋርያው ጳውሎስ ለሕይወቱ ዓላማ ነበረው (ፊልጵ. 3:13-14)። መጽሐፍ ቅዱስን በምታስተምርበት ጊዜ ዓላማ ሊኖርህ ያስፈልጋል። ለመሆኑ ዓላማ ለምን ይጠቅማል? ዓላማ የሌለው አስተማሪ ብዙ ነገሮችን ያምታታል፥ በደንብም ማስተማር ያዳግተዋል። ዓላማ የሌለው አስተማሪ ከአንዱ ርእስ ወደ ሌላው ስለሚዘል ተማሪዎቹ ምንም የተጨበጠ ትምህርት ሊያገኙ አይችሉም።

### የዓላማ ትርጉም:-

ዓላማ ማለት አስተማሪው በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ሊያስተላልፈው የሚፈልገው አጭር አሳብ ማለት ነው።

### ይህ ዓላማ :-

1. ለማስታወስ እንዳያስቸግር አጭር መሆን አለበት።
2. ለመጨበጥ እንዳያስቸግር ውስብስብ መሆን የለበትም።
3. ለመረዳት እንዳያስቸግር ግልፅ መሆን አለበት።

### አጠቃላይ ግቡ:-

መጽሐፍ ቅዱስን ለማስተማርና የክርስትና ዕድገትን ለማዳበር ሊሆን ይችላል። ሆኖም የእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ትምህርት የራሱ የሆነ ዓላማ ያስፈልገዋል። አስተማሪው ዓላማውን ለተማሪዎቹ መናገር አያስፈልገው

ይሆናል፥ ነገር ግን በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ ከዓላማው እንዳይወጣ መጠበቅ ይኖርበታል።

ለእያንዳንዱ ትምህርት የራሱ የሆነ ዓላማ ስታዘጋጅ የሚከተሉትን ሦስት ነጥቦች አትዘንጋ።

1. ስለምታስተምረው ትምህርት አስብ፥ ስለምን እንደምታስተምር ተረዳ፥ የተገለጹትን ፍሬ ነገሮች በሚገባ አጥና፥ የማስተማሪያውን መጽሐፍ መመሪያዎች ተከተል።
2. ስለ ተማሪዎችህ ሕይወት አስብ፥ ያጋጠማቸው ፈተና ወይም ልዩ ችግር ከደረሰባቸው ስለ ሁኔታው ተረዳ።
3. የተማሪዎችህን ዕድሜና ፀባይ ለማወቅ ሞክር፥ የሚማሩት ለምንድን ነው?

## ዓላማ በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላል።

1. እውቀትን ማስተላለፍ፤ ይህም ግልጽ የሆኑና የተወሰኑ ነገሮችን ስናስተላልፍ ነው። ለምሳሌ፡- ሐዋርያው ጳውሎስ በመጀመሪያው ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት የደረሰባቸው ቦታዎች ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የ66 መጻሕፍት ስሞችና ማን እንደጻፋቸው ወዘተ...ማስተማር ሊሆን ይችላል። በዚህ መሠረት የምትፈልገው ለተማሪዎቹ ስለተወሰኑ ነገሮች ለመንገር ከሆነ ዓላማህ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ነው ማለት ነው።
2. መንፈሳዊ ትምህርትን ማስተማር። ተማሪዎቹ ወደ ጠለቀ የክርስትና እውቀት እንዲገቡ ስንፈልግ ነው። ለምሳሌ፡- ተማሪዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል በይበልጥ እንዲያደንቁትና እንዲያከብሩት መምራት ወይም ተማሪዎቹን ስለ ትንሣኤ በማስጠናት የጠለቀ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። ትምህርትህ የተመጣጠነ እንዲሆን የምትፈልግ ከሆነ በዓላማህ ውስጥ ይህ ክፍል ሊኖርበት ይገባል።
3. የባሕሪ ለውጥ፡- ተማሪዎቹ በዕለታዊ ኑሮአቸው ውስጥ መልካም ፀባይ እንዲያሳዩ ወይም ወደ ተግባር ለመምራት የሚሰጥ ትምህርት ነው። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ያለ ሥርዓት በሚመላለስበት ጊዜ ተማሪዎቹ ማስታረቅን፥ ወይም መምከርንና ማረምን እንዲለማመዱ ለማስተማር ነው። ተማሪዎቹ በሳምንታዊው የቤተ ክርስቲያኒቱ የጉብኝት ፕሮግራም እንዲሳተፉ ማስተማር ነው። ፍላጐታችን ተማሪዎቹ የባሕሪ ለውጥ እንዲያሳዩ ነው። ይህንን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የምንፈልገው በምን ዓይነት መንገድ ነው? መልሳችን በዓላማችን ውስጥ ሊኖር ይገባል።

## ማጠቃለያ

እንደ ሒሳብ የመሳሰሉትን ትምህርቶች ስናስተምር ፍላጐታችን ተማሪዎቹ ዕውቀት እንዲቀስሙ ብቻ ነው። ሆኖም የጠለቀ መንፈሳዊ ዕውቀት እንዲያገኙና ያገኙትንም ትምህርት በሥራ ላይ እንዲያውሉት ከፈለግን የማስተማር ዘዴያችንን መለወጥ አለብን።

# ትምህርት አምስት
## የትምህርቱ መግቢያ ጥቅምና አዘገጃጀት
### መግቢያ

ትምህርቱ የሚከፈልባቸውን አምስቱን ክፍሎች ከልስ። ዓላማ ማለት ምን ማለት ነው? ለምንስ ያስፈልጋል? የተቀለፈ ክፍል ውስጥ ከመግባታችን በፊት ምን ያስፈልገናል? ለትምህርቶቻችን የምንጠቀምባቸው መግቢያዎች በመከፈቻ ቁልፍ ይመሰላሉ።

### ፍሬ አሳቦች

ይህ የትምህርታችን ክፍል ተማሪዎች በይበልጥ ቃሉን እንዲያጠኑ መገፋፋትና ለራሳቸው መልስ ለማግኘት እንዲደፋፈሩ ማድረግ አለበት። ታዲያ ይህ እንዲሆን ምን ማድረግ አለብን?

ሀ. እያንዳንዱ ተማሪ ትምህርቱን ለመከታተል ፍላጐት እንዲያድርበት አነቃቁት። የተማሪዎችህን ሁኔታ ተገንዝበህ ደስ ይላቸዋል ብለህ በምትገምታቸው ነገሮች ጀምር።

1. ጥያቄዎችን ጠይቅ። ለምሳሌ:- የምታስተምረው 2ኛ ዜና መዋዕል ምዕራፍ 18 ከሆነ ሰዎች ለምን ይዋሻሉ ብለህ ጠይቅ። ከችግር ለማምለጥ አንዳንዴ ውሸት ብንናገርስ? እስቲ ሚክያስ ያደረገውን እንመልከት።
2. ለጆሮአቸው አዲስ የሆነ ነገር ተናገር።
3. ጥሩ ምሳሌ ወይም ታሪክ ተጠቀም።
4. ሥዕል ወይም ካርታ ተጠቀም።

ለ. ማንኛውንም ነገር ብትጠቀም ተማሪዎቹ በድምፅ መልስ እንዲሰጡ ወይም እንዲናገሩ አድርግ።

ሐ. መግቢያው ከዓላማው ጋር የሚስማማ መሆን አለበት።

መ. አስተማሪው ተማሪዎቹን ከመግቢያ ቀጥታ ወደ ትምህርቱ ለመምራት መቻል አለበት።

ሠ. የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንበብ ለመጀመር የምትፈልግ ከሆነ ተማሪዎቹ በሚነበበው ክፍል ውስጥ ምን ምን ነገር እንዲያስተውሉ እንደምትፈልግ አስቀድመህ በጥያቄ መልክ አቅርብላቸው። ጥያቄዎችህን አታብዛ። እነርሱም ከተማሪዎቹ ዕድሜ ጋር የተመጣጠኑ መሆናቸውን አረጋግጥ።

ሡ. ለጠየቅሃቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ መቀበል አትርሳ።

1. ትክክለኛውን መልስ ማወቅና አለማወቃቸውን ለማረጋገጥ ይጠቅምሃል።
2. ሁሉም ተማሪ መልስ እንዲያዘጋጅ እንደምትፈልግ ለተማሪዎቹ በዚህ ታረጋግጣለህ።

ረ. ተማሪዎቹ የእነዚህን አሳቦች ጥቅምና ጉዳት እንዲረዱ የውይይት ጊዜ ስጣቸው። የመጽሐፍ ቅዱስን የንባብ ክፍል አስተማሪው እራሱ ያንብብ።

የምንባቡን ክፍል ነገርአቸው እያንዳንዱ በጸጥታ ለራሱ እንዲያነብ ያድርግ፥ ወይም ደግሞ እያንዳንዱ ተማሪ አንዳንድ ጥቅስ ያንብብ።

ሰ. የሚነበበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በጠቅላላ አንድ ተማሪ ብቻ እንዲያነብ የምንፈልግ ከሆነ ተማሪው ጥሩ አንባቢ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን።

## ማጠቃለያ

በየጊዜው አንድ ዓይነት የመግቢያ ዘዴ ብቻ መጠቀም አያስፈልግም። ይበልጥ አሳባቸውን የሚሰበስብና ፍላጎታቸውን የሚቀሰቅስ ዘዴ በጥንቃቄ ምረጥ። መግቢያው ረጅምና የተንዛዛ፥ እንዲሁም ከዓላማ ውጪ እንዳይሆን አስቀድሞ ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው። ለመግቢያ የሚሆኑ ጥሩ ምሳሌዎችን ለማግኘት፦

"ጥናት በዘዴ" የተባለውንና "የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለሴቶች" የተባሉትን መጻሕፍት አንብብ።

# ትምህርት ስድስት

## የትምህርቱ ሐተታ ጥቅምና አዘገጃጀት

## መግቢያ

"መክፈቻውን በመጠቀም በሩን ከከፈትን በኋላ" አሁን እንግዲህ ወደ ዋናው ትምህርታችን እንሄዳለን። መግቢያውንና ዋናውን ትምህርት ማዋሃድ ይኖርብናል፥ በመካከላቸው ልዩነት እንዳለ ማስታወቅ የለብንም። ይህም ማለት መግቢያ ካቀረብን በኋላ በቀጥታ ትምህርቱን መቀጠል አለብን ማለት ነው።

## ፍሬ ሓሳቦች

ወደ ማስተማሪያው ክፍል ስንገባ ዓላማችንን በአሳባችን ውስጥ ማሰላሰል በጣም ጠቃሚ ነው።

ሀ. በተሰጠው ምንባብ መሠረት የማስተማር ዘዴ

1. ተማሪዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስን የምንባብ ክፍል እንዲረዱ በተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች ተጠቀም። ለምሳሌ፦ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ጌታ ምን ያስተምረናል? ብለህ ጠይቅ።
2. ዓላማው የተመሠረተበትን አጠቃላይ መምሪያ እንዲረዱ ጠቁማቸው።
3. ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲቀበሉና እንዲመሰጡበት አድርጋቸው።
4. ስለ ብዙ ቁም ነገሮች ከመናገር ይልቅ አንድ ነገር በደንብ ተምረው እንዲሄዱ ማድረግ የተሻለ ነው፥ ስለዚህ በተወሰነልህ ጊዜ ውስጥ ያሰብካቸውን ነጥቦች ሁሉ ለማስተማር አትቸኩል።
5. የአስተማሪ ሥራ መናገር ብቻ ሳይሆን ተማሪዎቹ ደግሞ ያላቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግም ነው። መንፈስ ቅዱስ ተማሪዎቹን በመጠቀም የሌላውን ተማሪም ሆነ የአስተማሪውን አስተሳሰብ

ሊያሰፋ ይችላል።

6. ትምህርቱ ወደ ግል ሕይወት ማምራት አለበት። በትምህርቱ መሠረት በዕለታዊ ኑሮአቸው እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባቸው አስረዳቸው።

ለ. በውይይት የማስተማር ዘዴ

በውይይት ክፍለ ጊዜ:-

- ሁሉም ተባብሮ እውነትን ይመረምራል።
- ሁሉም በነገሩ ይሳተፋል።
- ሁሉም አሳቡን የመግለጽ መብቱ ይከበርለታል።
- የአሳብ አለመግባባት ቢኖር እንኳ በፍቅር መገለጽ አለበት።
- ጥያቄዎችም ሆኑ መልሶች በአስተማሪውና በተማሪዎች በኩል መቅረብ አለባቸው።
- አስተማሪው በማጠቃለል ወደ አንድ አቅጣጫ ለመምራት መሞከር አለበት።

ሐ. በመምህሩ ተናጋሪነት ብቻ የማስተማር ዘዴ

አንዳንድ አስተማሪዎች በሚከተሉት የተሳሳቱ ምክንያቶች ይህንን ዘዴ ብቻ ይጠቀማሉ።

- መናገር ማስተማር ነው ብለው ስለሚያስቡ፤
- ጊዜ ስለሚቆጥብላቸውና ያዘጋጁትን ትምህርት መጨረስ ማስተማር እንደሆነ ስለሚገምቱ፤
- ሌላ ዘዴ ስለማያውቁ፤
- ተማሪዎቹ እንዲካፈሉ ወይም እንዲመልሱላቸው ማድረግ ስለማይችሉ፤
- ተማሪዎቹን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ስለሚፈልጉ ምንም ዓይነት ሌላ ድምፅ ወይም ጥያቄ ከተማሪዎቹ እንዲቀርብ አይፈቅዱም።

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ይህ ዘዴ ጠቃሚ የሚሆንበት ወቅት ይኖራል፤ ይኸውም መምህሩ በሙያው የሠለጠነ ከሆነና በዚህ መንገድ ማስተማር አስፈላጊ ከሆነ ይህንን ዘዴ ሊጠቀም ይችላል። ለዚህ ደግሞ:-

1. አስተማሪው ትምህርቱን በደንብ ማወቅ አለበት።
2. ሲያስተምር በተመስጦ ማስተማር አለበት።
3. የግሉ በሆነ የማስተማር ዘዴ መጠቀም አለበት።
4. የራሱን አገላለጽ በመጠቀም ደምፁን ከፍና ዝቅ ማድረግ አለበት።
5. የድምፁ መጠን ለክፍሉ የተመጣጠነ መሆን አለበት።
6. ተማሪዎቹን እየተመለከተ ማስተማር አለበት።
7. በዓይን የሚታዩ ነገሮችን በምሳሌነት መጠቀም አለበት።
8. ጥሩ ምሳሌዎችን መጠቀም ያስፈልገዋል።

## ማጠቃለያ

እውነትን ለሰዎች ለማስተላለፍ ለሚቀርበው ትምህርት የተወሰነና ከሁሉ የበለጠው ዘዴ ይህ ነው የሚባል የማስተማሪያ መንገድ የለም። የተለያዩ ዓይነት የማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም የበለጠ ውጤት ያስገኛል።

# ትምህርት ሰባት

# የትምህርቱ ምክር ጥቅምና አዘገጃጀት

## መግቢያ

እስከ አሁን ድረስ ስለ ዓላማ፥ መግቢያና ሐተታ ተምረናል። ነገር ግን ትምህርቱን ከተማሪዎቹ ዕለታዊ ኑሮ ጋር አገናዝበን ካላስተማርን ያቀረብነው ትምህርት ውጤት አይኖረውም።

## ፍሬ አሳቦች

ሀ. አንድን የተወሰነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መተንተን አስቸጋሪ ላይሆን ይችላል፥ ነገር ግን ተማሪዎቹ በሥራ ላይ እንዲያውሉት መግለጽ የሚቻለው እንዴት ነው?

ይህንን በሁለት የተለያዩ መንገዶች ማድረግ ይቻላል።

1. ተማሪዎቹ ይህንን ትምህርት በሥራ ላይ እንዲያውሉት ማደፋፈር።
2. ተማሪዎቹ እራሳቸውን እንዲጠይቁ ማድረግ።

## ማደፋፈር

- አንዳንዶች በትምህርቱ መሠረት ይኖራሉ። ስለዚህ ይህንን ሁኔታቸውን እንዲገፉበት መምከር ያስፈልጋል።
- ሌሎች ደግሞ ትምህርቱን ሰምተው ለቃሉ አይታዘዙም፥ ስለዚህ እነዚህን ሰዎች መገሠጽ ያስፈልጋል።
- የተቀሩት ደግሞ በመጀመሪያ ትምህርቱን ይቀበላሉ፥ በኋላ ግን ራሳቸውን በመደለል በቸልተኝነት ይተውታል። ስለዚህ እነዚህን ሰዎች ስለ ድርጊታቸው ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል።

## ራሳቸውን እንዲጠይቁ ማድረግ

1. ከዕለታዊ ኑሮአቸው በመነሣት ልባቸውን ሊነኩ የሚችሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅተህ አቅርብ። ለምሳሌ፦ ዓላማህ መዋሸት ኃጢአት መሆኑን ማስተማር ከሆነ "አንተ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?" ብሎ መጠየቅ ተማሪው እራሱን እንዲጠይቅ ያደርገዋል። ዕድሜያቸው በአሥር ዓመት አካባቢ ለሆኑ ልጆች እናትህ ዕቃ እንድትገዛ ገንዘብ ሰጥታህ ወደ ገበያ ብትልክህና ባለ ሱቁ ወይም ሻጩ ትርፍ ገንዘብ ቢመልስልህ ይህንን ገንዘብ ምን ታደርገዋለህ? ብለህ ጠይቃቸው። በተጨማሪ ወጣቶች ደግሞ በጊዜ ከትምህርት ቤት ተመልሰው ወላጆቻቸውን በሥራ እንዲረዱ ማሳሰብ መልካም ነው።

2. ተማሪዎች ከተሳሳተ ዓላማ እንኳ ተነሥተው መልካም ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ በማሳሰብ ዓላማቸውን እንዲመረምሩ ማድረግ ወደ በለጠ ዕድገት ሊመራቸው ይችላል።

3. ተማሪዎቹ ጥያቄዎቻቸውን በትምህርቱ ዓላማ መሠረት እራሳቸው እንዲመልሱ ገፋፋቸው። መልስ የማይሰጡ ከሆነ ምናልባትም አሳቡን በግልጽ ካለማሳየት ሊሆን ስለሚችል ማብራሪያ ጥያቄዎችን ጨምር። ለእንደዚህ ዓይነት ዝግጅት በቂ ጊዜ መስጠት አለብህ። አንዳንድ ጊዜ ከትምህርቱ በኋላ በትምህርቱ ላይ የተመሠረቱ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተማሪዎቹን ወደ ውሳኔ ሊመራቸው ይችላል። በውሳኔያቸውም መሠረት ተግባራዊ እንዲሆኑ መርዳት እንጂ በቃላት ብቻ ተወስነው እንዲቀሩ ማድረግ አያስፈልግም። ለምሳሌ:-ዕለታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ የጥናት ፕሮግራም፥ በቤተ ክርስቲያን ሥር የሚካሄድ የወጣቶች ፕሮግራምና የወጣቶች የሰንበት ትምህርት፥ ወዘተ.... እንዲያቋቁሙ ማድረግ ለራሳቸው ሕይወት ብርታትን ሲያገኙ ለሌሎች ደግሞ በረከት ይሆናሉ። ለሚያከናውኑት ፕሮግራም ሪፖርት መጠየቅ አትርሳ። ትምህርቱን በትክክል ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማወቅ ወላጆቻቸውን፥ ጓደኞቻቸውን ወይም ጐረቤቶቻቸውን መጠየቅ ያስፈልጋል።

ለ. የትምህርቱ መደምደሚያ ጥቅምና አዘገጃጀት

መደምደሚያ ማድረግ ተማሪዎቹ ትምህርቱን በደንብ እንዲይዙት ይረዳቸዋል። ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ለምሳሌ:- ጥያቄዎችን፥ ቀላልና በጥንቃቄ የተዘጋጁ ፈተናዎችን በመጠቀም፥ የትምህርቱን አስተዋጽኦ እንደገና በመናገር፥ ታሪኩን እንደገና በመተረክና በግብር በማሳየት፥ ወዘተ... ክለሳ ማድረግ ይቻላል። በጥንቃቄ የተዘጋጀ የክለሳ ዘዴ የክለሳውን ፕሮግራም አስደሳች ያደርገዋል።

መደምደሚያ ቢያንስ ሦስት ተግባሮች ይኖሩታል።

1/ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል።

2/ ለተከታዩ ትምህርት መሠረት ይጥላል።

3/ ያልተብራራ ወይም ግልጽ ያልሆነ አሳብ ካለ አንዳንድ ፍንጮችን ይሰጣል።

በመደምደሚያው ውስጥ የትምህርቱን ዓላማና ሐተታ ማጠቃለል ያስፈልጋል። መደምደሚያውን ካበቃን በኋላ ተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዲያስታውሱትና ለተከታዩ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ ሊረዳቸው የሚችል የቤት ሥራ መስጠት ያስፈልጋል። የተወሰኑ ገጾችን ወይም ምዕራፎችን አንብበው ሊመልሱ የሚችሉአቸውን ጥያቄዎች መስጠት አንበቦ የመረዳት ችሎታቸውን ማዳበር ሲሆን መንፈሳዊ እውቀታቸውንም ማበልጸግ ሊሆን ይችላል።

## ማጠቃለያ

ትምህርቱን ከሕይወት ጋር ማገናዘብና በጥሩ ሁኔታ ማጠቃለል በጣም ጠቃሚ ነው። ምክርና ማጠቃለያ የሌለው ትምህርት ጨው የሌለበት ወጥ ነው። እንደዚህ ዓይነት ትምህርት ጣዕመ-ቢስ ነው ማለት ይቻላል።

# ትምህርት ስምንት

## የትምህርቱ ጥያቄዎች ጥቅምና አዘገጃጀት

በጥበብና በጥንቃቄ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ተማሪውንና ትምህርቱን እንዲገናኙ የሚረዱ መንገዶች ናቸው።

ሀ. የጥያቄ ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው።

1. ቀጥተኛ መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች:-

የቃል ትርጉም:- ለምሳሌ ደቀ መዝሙር ምን ማለት ነው?

አሻሚ መልስ የማይኖረው ጥያቄ:- ለምሳሌ የክርስቶስ የልደት ታሪክ በደንብ የተዘረዘረው በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው?

ማን? ምን? መቼ? የት? የሚሉ መጠይቆች መጠቀም:- እነዚህ መጠይቆች አንዳንድ ጊዜ ዝርዝር መጠይቆች ይባላሉ። ለምሳሌ:- መጥፎዎቹና መልካሞቹን የእስራኤል ነገሥታት በዝርዝር ጻፍ። ይህም ማለት:- መጥፎዎቹና መልካሞቹ የእስራኤል ነገሥታት እነማን ናቸው? ማለት ነው።

ክለሳ:- 66 ቱን ቅዱሳት መጻሕፍት በቅደም ተከተል ጻፍ።

2. አሳብ ለማመንጨት የሚረዱ ጥያቄዎች:-

እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ እንዲያስቡ፥ የሚመስላቸውን እንዲናገሩና ለማስረዳት የምንጠቀምባቸው ቀስቃሽ ጥያቄዎች ናቸው።

- እንዲያስቡ መቀስቀስ፤ ለምሳሌ:- በእሑድ ቀን የእግር ኳስ መጫወት ስሕተት ነውን?
- የጠለቀ እውቀት ለማስገኘት፤ "በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው።" ይህ ምን ማለት ነው? ወይም:- "ጠላቶችህን ውደድ" የሚለውን ቃል በሕይወታችን እንዴት ልንፈጽመው እንችላለን?

ለ. የጥያቄ አቀራረብን ማሻሻል።

1. የምታስተምረውን ትምህርት በሚገባ እወቅ። የማታውቀው ጥያቄ ሲገጥምህ አላውቅም ወይም ስለዚህ ጉዳይ በይበልጥ መመርመር አለብኝ ማለትን ተማር።
2. በደንብ ተዘጋጅ። ጥያቄዎችህን በደብተር ጽፈህ አዘጋጅ።
3. ጥያቄዎችህ አጫጭርና ግልጽ ይሁኑ።
4. አዎን ወይም አይደለም የሚል መልስ የሚሰጥባቸውን ጥያቄዎች አታብዛ።
5. አሳብ የሚያመነጩ ጥያቄዎችን በብዛት ስጥ። ተማሪዎቹም እንዲያስቡ በቂ ጊዜ ስጣቸው።
6. ጥያቄዎቹን ለመመለስ ተማሪዎቹ ሁሉ እንዲሳተፉ አድርግ። አስቀድመህ ጥያቄውን ጠይቅ። ከዚያም የሚመልሰውን ተማሪ ስም ጠርተህ አስነሣው። ነገር ግን ተማሪውን ካስነሣህ በኋላ ጥያቄውን

አትጠይቅ።

7. ጥያቄዎቹን ስታዘጋጅ የተማሪዎቹን ዕድሜና የእውቀት ደረጃ ተመልከት።

ሐ. የተማሪ ጥያቄዎች።

ተማሪዎች እንዲጠይቁህ አደፋፍራቸው እንጂ ጸጥ ብለው እንዲያዳምጡህ ብቻ አታድርግ። ከእነርሱ የሚመነጩትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ መጠባበቅ ይኖርብሃል።

ከተማሪው በኩል የመጣው ጥያቄ ትምህርቱን የሚመለከት መስሎ ከተሰማህ እንዲህ ብለህ ራስህን ጠይቅ፦

1. ለጠየቀው ተማሪ በጣም አስፈላጊ ነው?

2. ለመልሱ በደንብ መዘጋጀት ያስፈልጋል?

3. ጥያቄው ለሌሎች ተማሪዎች ይጠቅማል?

መ. ፈተና መስጠት

ስለ ክርስትና ሕይወት ካስተማርን በኋላ ተማሪዎቹ በሕይወታቸው ክርስቶስን እንደመሰሉና እንዳልመሰሉ ለማወቅ መጣር አለብን።

1. ሰዎች ትምህርታችንን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይከታተላሉ፥ ይፈትናሉ፥ ይገመግማሉ። በእኛና በትምህርት ክፍለ ጊዜያችን ላይ የሚሰጡት አስተያየት ምን ዓይነት ነው?

2. ተማሪዎቹም በቁጥር አንድ ላይ የተጠቀሰውን ነገር ያደርጋሉ። ስለዚህ ተማሪዎቹስ ስለ አስተማሪዎች ያላቸው አስተሳሰብ ምን ዓይነት ነው?

3. እግዚአብሔር ትምህርታችንን ይፈትናል፥ ይገመግማል። ጌታ በያዕቆብ 3፡1 "ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፥ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና" በማለት የተናገረው ቃል አይለወጥም። እግዚአብሔር እኛ ከምንሰጠው አፋዊ አገልግሎት በላይ ይፈልግብናል። ስለዚህ እንዴት እንደምናስተምር እና ምን እንደምናስተምር ማወቅና ተግባራዊ በማድረግ በጥንቃቄ ማስተማር አለብን። የሚፈለግብንን መሥዋዕት ሁሉ ከፍለን እርሱ የሚጠቀምብን መሆን እንጂ ከራሳችን የሥጋ ፈቃድ የመነጨ ፍላጎት ለአገልግሎታችን እንቅፋት ማስቀመጥ የለብንም። የእያንዳንዱም ሥራ በእሳት ስለሚፈተን በስንፍናና በድካም ማስተማር ትክክል አይደለም (1ኛ ቆሮ. 3፡10-15፥ 1ኛ ጴጥ. 5፡4)።

ሠ. በጥንቃቄ የተዘጋጀ ፈተና ።

1. መምህሩ ያቀረበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመመዘን ይረዳዋል።

2. የማስተማር ዘዴው መሻሻል የሚገባው ወይም የማይገባው መሆኑን ይጠቁማል።

3. ተማሪዎቹ የምንሰጠውን የክርስትና ትምህርት ምን ያህል በሕይወታቸው ውስጥ እንደተረጎሙት ይጠቁማል።

ረ. የጥያቄ ዓይነቶች

1. እውነት ወይም ሐሰት፤
2. በክፍት ቦታዎች የጐደለውን ሙላ፥
3. ትክክለኛውን መልስ ምረጥ፥
4. አዛምድ፤
5. የሚመስልህን መልስ ስጥ፥
6. በዝርዝር አስረዳ።

ከሚገኘው ነጥብ ይልቅ ትክክለኛ ሕይወት ስለሚበልጥ ተማሪዎች አንዱ የሌላውን መልስ በመቅዳት መልስ እንዳይሰጡ ማድረግ ተገቢ ነው።

## ማጠቃለያ

በፋብሪካዎችና በማምረቻ ድርጅቶች ውስጥ የምርቱን ጥራትና ጉድለት ለማወቅ መሻሻል የሚገባውን ለማሻሻል ብዙ የጥራት ቁጥጥሮችና ሙከራዎች ይደረጋሉ። አስተማሪዎችም እንዲሁ የሚያመርቱት መንፈሳዊ ሕይወት ጥራቱ የቱን ያህል እንደሆነ በተለያየ መንገድ መፈተን ይገባቸዋል። የፈተና አቀራረብ ዘዴዎችን መቀያየርና ማሻሻል ተገቢ ነው።

# ትምህርት ዘጠኝ

## የማስተማሪያ ስልቶችና መሣሪያዎች

### መግቢያ

ልጆች የሚማሩት፦

ከመቶ አሥር እጅ በመስማት፤

ከመቶ ሰልሳ እጅ በመስማትና በማየት፤

ከመቶ ሰባ እጅ በመስማት፥ በማየትና በመናገር፤

ከመቶ ዘጠና እጅ በመስማት፥ በማየት፥ በመናገርና በማድረግ ነው።

ይህ መሆኑን ካወቅን የምንሰጠው ትምህርት የበለጠ ውጤት እንዲኖረው ተገቢውን መንገድ መከተል ያስፈልጋል።

### ፍሬ አሳቦች

ሀ. ለማስተማር የሚረዱ መሣሪያዎች ምንና ምን ናቸው?

1. የአስተማሪ መምሪያ መጽሐፍ፦
   - ለሰንበት ትምህርት አስተማሪዎች፤
   - ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች፤
   - ለሴቶች አስተማሪዎች፤
   - ለወጣቶች አስተማሪዎች፥

   እነዚህ መጻሕፍት የሚያገለግሉት መምሪያ ለመስጠት ብቻ ነው። ስለዚህ አስተማሪው ለእያንዳንዱ ትምህርት የራሱን ዝግጅት በደብተር ላይ ማስፈር አለበት።

2. ካርታዎች:- የአገሮች፥ የጳውሎስ ጉዞዎች፥ እስራኤላውያን ከግብፅ እስከ ከነዓን ያደረጉት ጉዞና ወዘተ....።
3. ሠንጠረዦች:- የነገሥታት፥ የነቢያት፥ ወዘተ....።
4. ሥዕሎች:- ከመጽሐፍ ወይም በአስተማሪው የተሳሉ።
5. ጥቁር ሠሌዳና ጠመኔ:- ቢቻል የተለያዩ ቀለሞች ያላቸው ጠመኔዎች ማዘጋጀት።

ለ. ምሳሌዎች

ምሳሌዎችን የምንጠቀመው ለምንድን ነው? እስኪ እንወያይበት።

1. ለገለጻ:- አንድ ዕቃ ወደ ብርሃን ውስጥ እየገባ ሲሄድ በግልጽ እየታየ እንደሚሄድ ሁሉ እንዲሁ አሳቡን ግልጽ ለማድረግ ይረዳል።
2. ለማስረጃ:- ከዚህ በፊት ሌሎች ትምህርቱን እንዴት በተግባር እንደተረጐሙት ለመግለጽ ይረዳል።
3. ለመገፋፋት (ለማደፋፈር):- ተማሪዎች ሌላው ሊያደርገው ከቻለ እኔም እችላለሁ የሚል ድፍረት እንዲያድርባቸው ለማድረግ ይጠቅማል።
4. ለማጠናከር:- ተማሪዎች ትምህርቱን ለወደፊቱ እንዳይረሱት ለማድረግ ያገለግላል።
5. ለንቃት:- ተማሪዎች አሳባቸውን ሰብስበው ትምህርቱን በጉጉት እንዲከታተሉ ለማድረግ ይረዳል።

የምንናገራቸው ምሳሌዎች ከምናስተምረው ትምህርት ውጪ መሆን የለባቸውም። ምሳሌዎችን ማብዛት አስፈላጊ አይደለም። ለአንድ ትምህርት ቢበዛ ሁለት ምሳሌዎች በቂ ናቸው።

ሐ. ምሳሌዎችን ማግኘት የሚቻለው ከየት ነው?

ጌታ ኢየሱስ ከየት እንዳገኛቸው እንመልከት። ጌታ ኢየሱስ ምሳሌዎችን ያገኘው ከቤተሰብ አካባቢ፥ ከግብርና፥ ከመሥሪያ ቤት፥ ከፖለቲካ አካባቢ፥ ከግል ልምምድ፥ በጊዜው ካለው ሁኔታ፥ ከተፈጥሮ፥ ከሌሎች የሕይወት ታሪክና ከስብከቶች ነበር።

ምሳሌውን ከርእሱ ጋር አያይዞ በማስታወሻ ደብተር ውስጥ መጻፍና አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ለሌሎች ማካፈል ጠቃሚ ነው።

መ. ምሳሌዎችን የመጠቀም ዘዴ:-

1. ምሳሌውን ከማቅረብህ በፊት ጥቅሙን በሚገባ ተረዳ።
2. ምሳሌውን ስታቀርብ ተማሪዎቹ ጥቅሙን ያልተገነዘቡት ከመሰለህ ትርጉሙንም ግለጽላቸው።

ሠ. የጥቁር ሠሌዳ ጥቅም:-

1. በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ በጥቁር ሠሌዳው እንዴት እንደምትጠቀምበት ዕቅድ አውጣ። ለምሳሌ:- ለትምህርቱ አስተዋጽኦ፥ የተማሪዎችን አሳብ ለመዘርዘር፥ ካርታ ወይም ሥዕል ለመሳል፥ የከባድ ቃላትን ትርጉም ለማብራራት፥ ወዘተ....።
2. በጥቁር ሠሌዳ ላይ የምትጽፈው ጽሑፍ ለሁሉም መነበብ እንዲችል

ትላልቅና ግልጽ መሆን አለበት።

3. ቀላልና አጫጭር ዐረፍተ ነገሮችን መጠቀም የተሻለ ነው።
4. የምትጽፋቸውን ነገሮች በማስተማር ላይ ሳለህ ስትደርስባቸው በየተራቸው ወይም ተማሪዎቹ ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት ልትጽፍ ትችላለህ።
5. ከትምህርቱ ጋር ግንኙነት የሌለው ነገር ሁሉ ከሠሌዳው ላይ መጥፋት አለበት።
6. የጥቁር ሠሌዳውን ማጽጃና ሠሌዳውን በንጽህና ያዝ።

ረ. አጠቃላይ ምክሮች፦

1. ለማስተማር የሚጠቅሙህን ነገሮች አስቀድመህ በሥርዓት አዘጋጃቸው።
2. ለማሳየት የምትፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ ትላልቆችና ለሁሉም የሚታዩ መሆናቸውን አረጋግጥ። አንድ ነገር ይዘህ ለማሳየት ስትፈልግ በተከፈተ መስኮት አጠገብ አትቁም፥ ምክንያቱም በመስኮቱ በኩል ገብቶ በምታሳየው ነገር ላይ የሚያርፈው ብርሃን ተማሪዎቹ እንዳያዩት ሊያደርግ ይችላል።
3. ለማስተማር የምተጠቀምበት ነገር ዓላማው ምን እንደሆነ ተማሪዎቹ እንዲያውቁት አስረዳቸው።
4. ብዙ ዋጋ የሚያስወጣ ነገር አትፈልግ፥ ባለህ መሣሪያ ለመጠቀም ሞክር።
5. ለማስተማር የምትጠቀምባቸውን መሣሪያዎች ስታዘጋጅ ተማሪዎቹ እንዲረዱህ ጋብዛቸው።

## ማጠቃለያ

ትምህርትህን ጣፋጭና አስደሳች ለማድረግ ለምትከፍለው መሥዋዕትነትና ለምትደክመው ድካም ትምህርቱ በሚያስገኘው ያማረ ውጤት ትካሳለህ። ተማሪዎችህ እውቀት እንደገበዩ፥ አንተም እንዳስተማርክ ስትረዳ ልብህ በደስታ ይሞላል። ይህንም ነገር ሞክረህ እየው፥ ቀምሰህ ጣፋጭነቱን ተረዳ።

# ትምህርት አሥር

## ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት

1. ደኅንነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት

ደኅንነት ማለት "እሺ" ወይም "አምናለሁ" ብሎ መናገር ብቻ አይደለም። በመጀመሪያ ለማመን የሚፈልገው ሰው ማወቅ ያለበት ምን እንደሚያምንና ለማን "እሺ" እንደሚል ነው። ስለዚህ ደኅንነት ምን ማለት እንደሆነ ለሰውዬው ማስረዳት አስፈላጊ ነው። አንድ ሰው ስለ ደኅንነት ማወቅ ያለበት ሦስት ነገሮች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

ሀ. <u>እግዚአብሔር እንደሚወደው ማወቅ አለበት።</u>

ዮሐንስ 3፡16ን በመጥቀስ ለሰውዬው ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ንገረው። የእግዚአብሔር ፍቅር ከአባቱ፥ ከእናቱ፥ ከወንድሙና ከእህቱ ፍቅር ሁሉ እንደሚበልጥ ማወቅ አለበት። ይህንን ግዙፍ ዓለም የፈጠረው አምላክ ኢምንት የሆነውን እርሱን ይወደዋል። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ያውቃል። በግል ስለ እርሱ ያስባል።

ለ. <u>ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ማወቅ አለበት።</u>

ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ለማሳየት በሮሜ 3፡23ና 6፡23 ያለውን መመልከት ተገቢ ነው። ሁላችንም ኃጢአት ሠርተናል። ሁላችንም የራሳችንን መንገድ ተከትለናል። ሁላችንም ኃጢአተኞች በመሆናችን የእግዚአብሔርን ፍርድ እንጠብቃለን። ራሳችንን ከዚህ ፍርድ ለማዳን ብቃት የለንም።

ሐ. <u>እግዚአብሔር የደኅንነት መንገድ ማዘጋጀቱን ማወቅ አለበት።</u>

እግዚአብሔር ይህንን ደኅንነት እንደ ነፃ ስጦታ ሊሰጠን ይፈልጋል። ኢየሱስ ለእርሱ እንደ ሞተና አዲስ ሕይወት ሊሰጠው እንደሚችል ለማስረዳት እንደገና ዮሐንስ 3፡16ን መጠቀም መልካም ነው። ኢየሱስ የእርሱን የኃጢአት ቅጣት ተቀብሎለታል።

2. <u>ሰውዬው ይህን ደኅንነት እንዴት እንደሚቀበል ማሳየት</u>

ብዙዎች ጥሩ ሰዎች ከሆኑና ክርስቲያኖች የሚሠሩዋቸውን ሥራዎች ከሠሩ ክርስቲያን የሚሆኑ ይመስላቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ ወላጆቻቸው ክርስቲያኖችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመሆናቸው እነርሱም ክርስቲያኖች የሆኑ ይመስላቸዋል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ይህን አያስተምርም (ኤፌ. 2፡8-9)። ክርስቶስ ወደ ልቡ ገብቶ አዳኙ እንዲሆን ራሱ መጋበዝ እንዳለበት ለዚህ ሰው ማስረዳት ያስፈልጋል። ኢየሱስም ወደ ልቡ ገብቶ ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ እንደሚያደርገው ማመን አለበት።

ኃጢአቱን በመናዘዝ ኢየሱስ ይቅር እንዲለው መጸለይ እንዳለበት መንገር ተገቢ ነው። ኢየሱስ ለእርሱ ሲል እንደሞተና አዲስ ሕይወት ሊሰጠው ከሞት እንደተነሣ ማመኑን እርሱ ራሱ መናገር አለበት። ሰውዬው ክርስቶስን ለመቀበል በፈቃደኝነት ከወሰነ በአንድ ሰው መሪነት አጭር ጸሎት ቢያደርግ መልካም ነው፥ ከዚህ በኋላ ወዲያውኑ እምነቱን ሳይደብቅ በሰዎች ፊት እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባዋል።

3. <u>አዲሱን አማኝ ማበረታታት</u>

አንድ ሕፃን ሲወለድ ወላጆቹ ለራሱ ጥንቃቄ እንዲያደርግ አይተውትም። ገና ከፉውንና ደጉን ለይቶ ስላላወቀ እንደዚህ ማድረጉ ሕፃኑን ለሞት አሳልፎ መስጠት ነው። ግን ወላጆች ሕፃኑ እንዲያድግና እንዲጠነክር የተለየ ጥንቃቄ ይወስዱለታል። ለአዲስ አማኝም የሚደረገው ተመሳሳይ ነገር ነው። በአዲስ ሕይወት ውስጥ መጽናናት ያስፈልገዋል። ይህም በእምነት እንዲያድግና ጠንካራ ክርስቲያን እንዲሆን ይረዳዋል።

## አዲሱ አማኝ ኢየሱስ ክርስቶስን በሚቀበልበት ጊዜ ማበረታቻ ያስፈልገዋል።

ስለ ደኅንነት ማረጋገጫ ለመስጠት ከመጽሐፍ ቅዱስ ዮሐ. 1፡12ን በአንድነት ማንበብ ያስፈልጋል። ማንበብ የማይችል ከሆነ ሌላ ሰው እንዲያነብለት ጥቅሱን በትንሽ ወረቀት ላይ ጽፎ መስጠት ይጠቅማል፥ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምልክት ማድረግ ይቻላል።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ውይይት ማድረግ ጠቃሚ ነው። ኢየሱስን የጠየቅኸው ምን እንዲያደርግልህ ነው? አሁን ድኗል? እግዚአብሔር ከልጆቹ አንዱ አድርጐሃል? እንዴት ታውቃለህ? እርግጠኛ ካልሆነ ዮሐንስ 1፡12 ወይም ዮሐንስ 5፡24 ይነበብለት። አዲስ አማኝ በክርስቶስ ማመኑን ማረጋገጥ አለበት። የዳነውም ክርስቶስ እንዲያድነው በመጠየቁ ነው። አንድ ሰው መልካም ለመሥራት በመሞከር ክርስቲያን ሊሆን አይችልም።

ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጐ መቀበሉን ለሌላ ክርስቲያን እንዲናገር ማበረታታት ያስፈልጋል። ለወላጆቹ፥ ለባለቤቱ፥ ለልጆቹ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክርላቸው እነርሱ ይህንን ነገር ገ[illegible] ለመጀመሪያ ጊዜ መስማታቸው ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በእርሱ ምስክርነት እግዚአብሔር ወደ እርሱ ሊያቀርባቸው ይችላል። መስካሪው በተከ[illegible]ቹ ሳምንታት ውስጥ ሳያቋርጥ አዲሱን አማኝ መጐብኘት አለበት። ጌታ ኢየሱስ ለእርሱ ረዳት መሆኑን ማሳሰብ ያስፈልጋል። ዕብ. 13፡5 እንዲህ ይላል፡- "አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፥" ኢየሱስ ይህን ተስፋ ስለሰጠን ቃሉን አያጥፍም። ዮሐንስ 3፡16ንና ዕብራውያን 13፡15ን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ምልክት ማድረግ ወይም በወረቀት ላይ ጽፎ ወደ ቤቱ ይዞ እንዲሄድ ማድረግ መልካም ነው።

1ኛ ዮሐ. 1፡9ን አስረዳው። ኢየሱስ አዳኙ ሆኖ ወደ ሕይወቱ መጥቶአል። ኢየሱስ ሕይወቱን ሊቆጣጠርና ከኃጢአት ሊጠብቀው ይፈልጋል። አዲሱ አማኝ በኢየሱስ ርዳታ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር ለማድረግ መሞከር አለበት። ቢሳሳት የእግዚአብሔር ልጅነቱ ይቀራል? አይቀርም፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ኅብረቱ ንስሐ እስከሚገባበት ጊዜ ድረስ ይቋረጣል። እንደገና መዳን ያስፈልገዋልን? አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ አያስፈልገውም። በኃጢአቱ ቢፀፀትና ቢናዘዝ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው ዝግጁ ነው። ከእርሱም ጋር ያለው ኅብረት ይታደሳል።

መስካሪው ለዚህ አዲስ አማኝ በሚያስፈልገው ጊዜ ርዳታ ሊሰጠውና በየቀኑ ሊጸልይለት ኃላፊነት አለበት።

ማሳሰቢያ፡- ይህንን መመሪያ ሰዎች ልጆቻቸውን ወይም ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

## ለክፍል አንድ የተዘጋጁ የክለሳ ጥያቄዎች

1. በዚህ በመጀመሪያ ክፍል ከኢየሱስ የማስተማር ዘዴ ምን ምን መማር እንችላለን?
2. የምናስተምረው ትምህርት ከሕይወታችን ጋር መመሳሰል ያለበት ለምንድን ነው?
3. ትምህርት ስናስተምር ተማሪዎች ከሚያውቁት ነገር ጀምረን ወደ

ማያውቁት መሸጋገር ያለብን ለምንድን ነው?

4. ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የምንችለው እንዴት ነው?

5. ተማሪዎች ከተማሩአቸው ትምህርቶች መካከል አንዱን ርእስ መርጠው እንዲያስተምሩ አድርግ።

# ክፍል ሁለት

## ሴቶችን የማስተማር ዘዴ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህራን የሴቶችን ስብሰባዎች እንዴት እንደሚያቅዱ፥ እነርሱን እንዴት እንደሚያደራጁአቸውና እንደሚያስተምሯቸው ማወቅ ይገባቸዋል። ስለዚህ መምህራንን ለመርዳት "አገርዋና ቤትዋ" ከተባለው መጽሐፍ የሚከተሉትን ትምህርቶች አዘጋጅተንላችኋል፥ በተጨማሪ እያንዳንዱ መምህር ይህን መጽሐፍ ማንበብ ይገባዋል።

## መግቢያ

## ክርስቲያን ሴቶች ለኅብረተሰቡ ያላቸው መንፈሳዊ አገልግሎት

ሴቶች ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክቱት የራሳቸው የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት አላቸው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለይ የሐዋርያት ሥራን ስናጠና ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የተመሠረተችው በክርስቲያኖች የግል መኖሪያ ቤት ውስጥ መሆኑን እንረዳለን። ዳግመኛ የተወለዱ፤ በጌታ የጸኑ ጠንካራ የሆኑ ክርስቲያን ቤተሰቦች የቤተ ክርስቲያን ጽኑ መሠረት ናቸው።

ስለዚህ እንደ አንድ ጥሩ ምሳሌ አድረገን ልንጠቀምበት የምንችለው አቂላና ጵርስቅላ የተባሉትን ባልና ሚስት ታሪክ ነው። እነዚህ ጠንካራ የአይሁድ አማኞች በቆሮንቶስ ከተማ ውስጥ ባለች መንደር ሲኖሩ በገዛ ቤታቸው በጀመሩት ምስክርነትና አገልግሎት ብዙ ጣዖት የሚያመልኩ አሕዛብን ወደ ጌታ መልሰዋል። በቆሮንቶስም ከተማ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርታለች።

አንድ ሰው ቤት ሲሠራ በመጀመሪያ መሠረት ለመጣል መሬቱን ይቆፍራል፥ ግድግዳና ምሰሶ ያቆማል፥ አስተባብሮ የሚያያይዝ ማገር ይመታል፥ ጣሪያ ያበጃል፥ ቤቱም ሙሉ መልክ እንዲያገኝ የጭቃ ወይም የቆርቆሮ ክዳን ያለብሳል፥ ከዚህ በኋላ የተሟላ ቤት ይሆናል። እንዲሁም ወንዶችና ሴቶች ተባብረው በአንድነት ሲሠሩ የቤተ ክርስቲያን ሙሉ ኃይል ይሆናሉ። የክርስትና ሕይወታችን በመጀመሪያ ደረጃ በቤተሰባችን ውስጥ መሠረት ካላለው ልጆቻችንን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመላክና ራሳችንም በየሳምንቱ በመሄዳችን ብቻ ጽኑ ሊሆን አይችልም።

አብዛኛዎቹ ክርስቲያን ሴቶችና የቤት እመቤቶች የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተፈቀደው ለወንድ፥ ለልጆች፥ ለሰባኪዎች፥ ለአባት፥

ለወንጌላውያን፥ ለመጋቢያን፥ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ለመሳሰሉት ብቻ ስለሚመስላቸው ሴቶች የአገልግሎት ድርሻ እንደሌላቸው አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ አስተሳሰብ ለቤተሰብ እንቅፋት ሲሆን፥ ለቤተ ክርስቲያን ደግሞ ውድቀት ነው። ሴቶችም በእርግጥ የሥራ ድርሻ አላቸው።

ማንኛዋም ክርስቲያን ሴት በተለይ የቤት እመቤት:-

ሀ. በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ክብር አገልግሎት ትሰጣለች።

ለ. ለቤተሰብ መሠረት ናት።

ሐ. ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት አስተዋጽኦ ታደርጋለች።

መ. ለኅብረተሰብም የምታበረክታቸው የተለያዩ የሥራ ድርሻዎች አሏት። እነዚህ ነጥቦች "አገርዋና ቤትዋ" በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ በሰፊው ስለተዘረዘሩ መምህራን ይህንን መጽሐፍ ቢጠቀሙበት መልካም ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሠረትና የክርስትና ሕይወታችን ጽናት የሚያገኘው በመጀመሪያ በራሳችን ቤት ውስጥ መሆኑን በትክክል ከተገነዘብን ቤተሰባችንንና ቤተ ክርስቲያናችንን በደስታ እናገለግላለን (ኢያ. 1:9)።

# ትምህርት አንድ

## የሴቶች ስብሰባ- ክፍል አንድ

1. <u>የሴቶች ስብሰባ መመሪያ</u>

ሀ. የሴቶች ሰብሰባ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ከምታስተምርበት ፐሮግራም መካከል አንዱ ነው።

ለ. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሴቶች ስብሰባ የሚመራው በሽማግሌዎች ነው።

ሐ. አስተማሪዎች በቤተ ክርሰቲያን ሽማግሌዎች የሚመደቡ ሰዎች ናቸው።

መ. የሴቶች ስብሰባ ከቤተ ክርሰቲያን ኅብረት የተገነጠለ አካል መሆን የለበትም።

ሠ. ሽማግሌዎች በሌላ ቦታ እንዲደረግ ካልወሰኑ በስተቀር የሚካሄደው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ነው።

2. <u>የሴቶች ስብሰባ ዓላማ</u>

ሀ. <u>ለአምልኮ</u>

1. ሴቶች እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በይበልጥ እንዲረዱና

2. እግዚአብሔርን ማመስገንና ማወደስ እንዲማሩ ይረዳቸዋል።

ለ. <u>ለኅብረት</u>

1. ሴቶች

ሀ/ ቃሉን በማጥናትና

ለ/ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን አንድነት ለማጠናከር

ይረዳቸዋል።

2. ሴቶች

ሀ/ እርስ በርስ ሸክማቸውን በመሸካከም እንዲጸልዩና

ለ/ ግብዝነት በሌለበት ፍቅር እርስ በርስ እንዲቻቻሉ ይረዳቸዋል።

ሐ. ለምስክርነት

1. ሴቶች

ሀ/ ለባሎቻቸው ታዛዦችና አክባሪዎች በመሆን፤

ለ/ ቤታቸውን በንጽሕና በመጠበቅና እንግዳ በመቀበል፤

ሐ/ ልጆቻቸውን በመምራትና በሥነ ሥርዓት በመቅጣት ለቤታቸው ታማኝ ምስክሮች እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

2. ሴቶች

ሀ/ በአኗኗራቸው መልካም ምሳሌ በመሆን፤

ለ/ የስብሰባ ቀናትና ሰዓትን በማክበር፤

ሐ/ ለመሪዎች፥ ለመጋቢዎችና ለሽማግሌዎች በመጸለይና

መ/ መከፋፈልን ከሚፈጥሩ ነገሮች ራሳቸውን በመጠበቅ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ታማኝ ምስክሮች እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

3. ሴቶች

ሀ/ ላልዳኑት ስለ ክርስቶስ በመናገርና

ለ/ ታማኞችና ሐቀኞች በመሆን ለኅብረተሰባቸው ምስክሮች እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

መ. ለአገልግሎት

1. ሴቶች

ሀ/ የታመሙትን፥ አቅመ- ደካሞችን፥ ድሆችንና ችግረኞችን በመርዳት ያገለግላሉ።

ለ/ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ምግብን በማዘጋጀት፥ ቤተ ክርስቲያንን በማጽዳትና የመሳሰሉትን ሥራዎች በመሥራት ተገቢ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

ሐ/ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላውያን እንድትልክ ለማድረግ ወይም በሽማግሌዎች የተወሰነውን ሥራ በተግባር ላይ ለማዋል ገንዘብ ያወጣሉ።

3. <u>የእያንዳንዷ ክርስቲያን ሴት ኃላፊነት</u>

ሀ. <u>በግለሰብ ደረጃ</u>

- በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራሞችና የጸሎት ስብሰባዎች መካፈል፤
- በቅዱስ ቁርባን ሥነ ሥርዓት ላይ መገኘት፤
- ከተለያዩ የጥንቆላና ልዩ ልዩ የባዕድ አምልኮዎች መለየትና
- ለቤተሰቧ እንክብካቤ ማድረግና በክርስትና ሕይወቷ ማደግ

ይጠበቅባታል።

ለ. <u>በኅብረተሰብ ደረጃ</u>

- በቤትዋም ሆነ በመንደርዋ ኑሮ በሚቻላት ሁሉ ተሳትፎ ማድረግ ይገባታል፥ ለምሳሌ:- የጤና አጠባበቅ፥ የቤት አያያዝና የእጅ ሥራ በማስተማር ድርሻዋን ልትወጣ ትችላለች።
- ችግረኞችን በመጐብኘትና ላልዳኑት ስለ ክርስቶስ በመመስከር በወንጌል ሥርጭት ውስጥ ልትሳተፍ ትችላለች።

# ትምህርት ሁለት

## የሴቶች ስብሰባ - ክፍል ሁለት

1. <u>የሴቶች ስብሰባ ጥቅም</u>

ሀ. ክርስቲያን ሴቶች በአጠቃላይ <u>የኅብረት ጊዜ</u> እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

1. የክርስቲያኖች ኅብረት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ይረዳቸዋል።
2. የክርስቲያኖች ኅብረት ችግራቸውን ለመካፈል ዕድል ይሰጣቸዋል።
3. የክርስቲያኖች ኅብረት አንዱ ለሌላው እንዲጸልይ ያስተምራል።

ለ. እግዚአብሔር ክርስቲያን ሴቶች በምን ዓይነት መንገድ እንዲኖሩ እንደሚፈልግ <u>መማር</u> ያስፈልጋቸዋል።

1. እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚታዘዙ፤
2. በመንፈሳዊ መንገድ እንዴት እንደሚያድጉና
3. እግዚአብሔር ለእነርሱ ዕቅድና ዓላማ እንዳለው ማወቅ አለባቸው።

ሐ. ክርስቲያን ሴቶች <u>የምስክርነትን</u> አስፈላጊነት መገንዘብ አለባቸው።

1. እግዚአብሔር ሌሎች ወንጌልን እንዲሰሙ የሚጠቀምበት መንገድ ምስክርነት ነው።
2. ለሌሎች መመስከር የራስን የክርስትና ሕይወት ያጠነክራል።
3. ለሌሎች መመስከር ቤተ ክርስቲያንን ያሳድጋል።

መ. ክርስቲያን ሴቶች በአጠቃላይ <u>ስለ አገልግሎት</u> መማር አለባቸው።

1. በማናቸውም ጊዜ ሌሎችን ለመርዳት እንዲችሉ ማበረታቻ ሊሰጣቸው ይገባል።
2. ሴቶች ሌሎችን ለማገልገል የክርስቶስን ምሳሌ መከተል እንዲችሉ መማር አለባቸው።
3. እርስ በርስ አገልግሎት መስጠት ለአገር ጠቃሚ ነው።

ሠ. ክርስቲያን ሴቶች ልጆቻቸውን የእግዚአብሔርን ቃል <u>ማስተማር</u> አለባቸው።

1. ልጆቹ ዕድሜያቸው ስድስት ዓመት ከመሙላቱ በፊት ብዙ መሠረታዊ ነገሮችን ሊማሩ ይችላሉ።
2. ልጆች እናቶቻቸው ከሚያሳዩት አርአያነት ትምህርት ይማራሉ።
3. እናቶች የልጆቻቸው ዋና አስተማሪዎች ናቸው።

2. <u>በስብሰባ ወቅት ሴቶች</u>

ሀ. ስብሰባው ሲጀመር ለመገኘትና እስኪያልቅ ለመቆየት መወሰን፥

ለ. በስብሰባው ጊዜ ልጆቻቸውን እንዲጠብቁላቸው ተለቅ ካሉ ልጆች ጋር ወይም ከጐረቤቶቻቸው ጋር መመካከር፥

ሐ. የያዙት ሕፃን ካለቀሰ ወዲያውኑ ወደ ውጭ ማውጣት፥

መ. ዘግይተው ከመጡ ቃሉ ተነብቦ እስኪያልቅ ወይም ጸሎቱ እስኪፈጸም በጸጥታ ልጁን ይዘው በውጭ መቆየት፥

ሠ. በስብሰባው ላይ መሪው የሚናገረውን ማዳመጥና ስለ ትምህርቱ ማሰላሰል፥

ረ. ማድረግ የሚገባቸውን ነገር ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት ማድረግ እንጂ በስብሰባው ወቅት ወጣ ገባ አለማለት፥

ሰ. በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጊዜ ንቁና ዝግጁ መሆን፤ ትምህርቱ ሲሰጥ ድካም እንዳይሰማቸው ቀደም ብለው በቂ ዕረፍት መውሰድና

ሸ. መነጋገርና ሹክሹክታ ሌሎች እንዳይሰሙ ስለሚያደርግ በፀጥታ ማዳመጥ ይገባቸዋል። እግዚአብሔር ለምናደርገው ነገር ሥርዓት እንዲኖረን ይፈልጋል (1ኛ ቆሮ 14:10)።

# ትምህርት ሦስት

## የስብስባ መሪዎች መመሪያ

ሀ. <u>የሚከተሉት ነገሮች ጥሩ መሪ መሆን የሚያስችሉ ናቸው።</u>

1. ራስን "በጣም ጥሩ መሪ መሆን እንዴት እችላለሁ?" ብሉ መጠየቅ።
2. በመጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ ራስን በእርሱ ቁጥጥር ሥር ማድረግ፤ እግዚአብሔር በሁሉም ነገር እንዲመራን መጠየቅና እንደሚፈጽመውም ማመን ተገቢ ነው።
3. የሴቶች ስብሰባ የቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም ክፍል በመሆኑ በየጊዜው ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሪፖርት በመስጠት እንዲጸልዩበት ማድረግ።
4. ለትምህርቱ ዝግጅትና ዕቅድ በቂ ጊዜ እንዲኖር በሌላ ሥራዎች ጊዜን አለማባከን።
5. የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎችን ዘወትር በደስታ መካፈል፤ ተማሪዎችም አዘውትረው እንዲመጡ ማደፋፈር።
6. ለእያንዳንዱ ተማሪ ዘወትር መጸለይ። በዚህ መንገድ ስለ እነርሱ የሚሰማን ስሜት እየጨመረ ይሄዳል።

7. ሁሉን በእኩልነት ማስተናገድ።

8. የሁሉንም ችግር በትዕግሥት ለመካፈልና ከእነርሱ ጋር ለመጸለይ ፈቃደኛ መሆን።

9. በየጊዜው ስብሰባ እንዲካፈሉ ማበረታታት፤ በጸሎትና በውይይት ተካፋይ እንዲሆኑ ማደፋፈር።

10. የሚመሩት ተማሪዎች የመሪዎችን ምሳሌነት እንደሚከተሉ አለመዘንጋት።

11. የስብሰባን ዓላማዎች አለመዘንጋት።

ለ. <u>ስብሰባዎችን የማቀድ ዘዴ</u>

1. በመጀመሪያ የስብሰባውን ተሳታፊዎች ሁኔታና የዕለቱን ትምህርት ዓላማ መረዳት አስፈላጊ ነው።

2. መሪው እያንዳንዱን ክፍል በአጠቃላይ በመመልከት ካልተዘጋጀ ትምህርቱ ሊበላሽ ይችላል።

3. አንድ ትምህርት እንዳስተማርን ወዲያውኑ የሚቀጥለውን ማዘጋጀት መጀመር ተገቢ ነው። ለዝግጅቱም በቂ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል።

4. የሚዘመሩትን መዝሙሮች አስቀድሞ መምረጥ አስፈላጊ ነው። መዘምራን ለትምህርቱ የሚያዘጋጁ መዝሙሮች አስቀድመው መምረጥ ይገባቸዋል።

5. ለሰዎች ችግር ጸሎት ማድረግ ያስፈልጋል።

6. የትምህርቱን ዓላማ አስቀድሞ ለራስ ከተማሩ በኋላ ሌሎችን ማስተማር ይገባል። ይህንን በጥልቅ ለመረዳት በጸሎት ጊዜ ሁሉ ማሰብና ማሰላሰል ተገቢ ነው።

7. ሁሉም ነገር በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተጠቃልሎ እንዲያልቅ በማድረግ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

ሐ. <u>የጥሩ መሪ አቋም</u>

1. አለባበስ

   ሀ. አቋምን ለማሳመር ጥንቃቄ ማድረግ፥

   ለ. በብዙ ዋጋ የተገዛ ልብስ ሳይሆን ንጹሕና በደንብ የተጠበቀ ልብስ መልበስና

   ሐ. ልብሳችን ወይም ጌጣጌጣችን ሰዎች ከትምህርቱ ይልቅ በእኛ ላይ እንዲያተኩሩ እንዳያደርጋቸው መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው።

2. አቋቋም

   ሀ. ቀጥ ብሎ መቆምና ጠረጴዛውን አለመመርኮዝ መልካም ነው። አለበለዚያ ሰዎች ስለ እኛ እንጂ ስለ ትምህርቱ አያስቡም።

   ለ. አንገት አለመድፋት።

3. አነጋገር

   ሀ. በችኮላ ሳይሆን በዝግታ መናገር፥

ለ. በስተኋላ የተቀመጡት ሁሉ እንዲሰሙ ድምፅን ከፍ ማድረግ፥

ሐ. በንግግር ጊዜ ሰዎችን መመልከት፤ አሳባቸውን ለመያዝ ዓይን ዓይናቸውን መመልከት፥

መ. ለመናገር ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች መምረጥና እንዴት መናገር እንደሚቻል ማቀድ፤ ያልተለመዱ ቃላትንም አለማብዛት መልካም ነው።

# ትምህርት አራት

## የስብሰባ መሪ ዝግጅት - ክፍል አንድ

የሚቀጥለው እያንዳንዱን የሴቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ያብራራል። ትምህርቱን እንዴት ለማስተማር እንደሚቻል ለማወቅ ይህን በጥንቃቄ ማጥናት ያስፈልጋል።

ሀ. <u>የመምህሩ የጥናት ክፍል</u>

1. ለጥናቱ የተሰጡትን ጥቅሶች ሁሉንም ቢያንስ ሦስት ጊዜ ማንበብ።
2. ምንባቡን በመመርኮዝ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስን መጠየቅ ጠቃሚ ነው።

   ሀ. ያነበብኩት ስለ ማን ነው?

   ለ. የሚናገረው ስለ ምንድን ነው?

   ሐ. ታሪኩ የተፈፀመው የት ነው?

   መ. መቼስ ነው?
3. ፍሬ ነገሮችን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።
4. የቃላትን ሁሉ ትርጉም መረዳት ተገቢ ነው።
5. የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶችንም በዚህ ሁኔታ በየቀኑ ማንበብ አስፈላጊ ነው።
6. በጠቅላላ ትምህርቱን ለመረዳት እንዲቻል የእግዚአብሔርን ርዳታ በጸሎት መጠየቅ ይገባል።
7. ትምህርቱን በአጠቃላይ ለመረዳት የተዘጋጀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ደጋግሞ ማንበብ ያስፈልጋል።
8. ለትምህርቱ የተዘጋጀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በክፍል ውስጥ እንዲነበብ ማድረግ መልካም ነው።

ለ. <u>ዓላማው</u>

1. ዓላማው በትምህርቱ ውስጥ መደረግ ያለበትን ነገር ይነግረናል።
2. ዓላማው እውቀትን ከመስጠትም አልፎ ተማሪዎች አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉም ያሳስባል።
3. እያንዳንዱ ትምህርት ዓላማውን ከዓላማው ወጪ ማድረግ የለበትም፡
4. ዓላማው የትምህርቱን አቅጣጫ ስለሚያሳየን አጥብቀን መከተል ይገባናል።

5. ትምህርቱ በሚዘጋጅበት ጊዜ ስለ ዓላማው ማሰብ ጠቃሚ ነው።
6. የትምህርቱ ዓላማ ለክፍሉ ግልጽ መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ነው።

ሐ. <u>የቃል ጥናት ጥቅስ</u>

1. የትምህርቱን ዋና አሳብ ይሰጣል።
2. በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ስለሆነ ተማሪዎቹ በቃላቸው ሊያጠኑት ይገባል።
3. ተማሪዎቹ የሚችሉ ከሆኑ የእያንዳንዱን ትምህርት የቃል ጥናት ጥቅስ ማጥናት ይጠቅማቸዋል።
4. የማይችሉ ከሆኑ ግን አንዱን ጥቅስ በጥሩ ሁኔታ ማጥናት ጠቃሚ ነው።
5. ጥቅሶችን ሲያጠኑ በሚገባቸው መንገድ ቢያጠኑ መልካም ነው።

መ. <u>የክለሳ ጥያቄዎች</u>

1. ያለፈውን ትምህርት በመመርኮዝ አንድ ወይም ሁለት ጥያቄዎች ይጠይቁ።
2. ከጥያቄዎቹ መካከል አንዳንዶቹ የሴቶችን አሳብ የሚያነሣሡ ቢሆኑና በተሰጡትም መልሶች ላይ ውይይት ቢካሄድ መልካም ነው።

# ትምህርት አምስት

## የስብሰባ መሪ ዝግጅት - ክፍል ሁለት

ሠ. <u>መግቢያ</u>

1. መግቢያ የክፍሉን አሳብ ለመሰብሰብ ይጠቅማል።
2. አጭር ታሪክ ወይም ጥያቄ ቢሆን መልካም ነው።
3. የመስማት ፍላጎታቸውን ያነሣሣል።
4. ሰዎችን ለትምህርቱ ያዘጋጃል። የትምህርቱን አሳብ ግልጽ ለማድረግ ይረዳል።
5. ከትምህርቱ ምን መጠበቅ እንደሚችሉ ያስገነዝባል።
6. ተማሪዎች ሊረዱት እንዲችሉ መግቢያ ግልጽ መሆን አለበት።

ረ. <u>ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን ክፍል ማብራራት</u>

1. ላለመሳሳት የታሪኩን ይዘት በደንብ ማጥናትና ማስታወሻ መጻፍ ያስፈልጋል።
2. የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ በሚጣፍጥ መንገድ ማቅረብ ያሻል። ይህም ትምህርቱን ማራኪ ያደርገዋል።
3. ኃይል ያለው በቃሉ ውስጥ ስለሆነ በተሰጠው መመሪያ መሠረት ጥቅሶቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጠቃሚ ነው።
4. አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ብዙ ዓይነት ትምህርት

ሊያስተምሩ ስለሚችሉ የትምህርቱን ዓላማ አለመልቀቅ ተገቢ ነው።

ሰ. <u>መደምደሚያ</u>

1. ይህ ከትምህርቱ ምን መማር እንዳለባቸው ይነግራል።
2. በአንድ ትምህርት ውስጥ ብዙ አሳቦችን መደባለቅ በተማሪዎቹ ላይ የአሳብ መዘበራረቅ ስለሚያመጣባቸው ምንም ሳይማሩ ሊወጡ ይችላሉ። ስለዚህ የትምህርቱን ዓላማ መጠበቅና አዲስ አሳብ አለማምጣት ተገቢ ነው።
3. መምህሩ ብቻ ከሚናገር ተማሪዎቹ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አሳባቸውን እንዲገልጹ በማድረግ ማስተማር ጥሩ ውጤት ያስገኛል።
4. ትምህርቱን እንዴት በተግባር እንደሚተረጉሙት ማስረዳት ያስፈልጋል።

ሸ. <u>የጸሎት ጊዜ</u>

1. መጸለይ የሚገባቸው መምህራን ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ናቸው።
2. ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው ለማያውቁት ሰዎች በኅብረት መጸለይ አስፈላጊ ነው።
3. ዘወትር እንዲጸልዩ ማበረታታትና የጸሎት ጥያቄዎቻቸውንም መቀበል ጠቃሚ ነው።
4. ስለ ጸሎት መልሶች እግዚአብሔርን ማመስገን ተገቢ ነው።
5. የእግዚአብሔርን ስም በአንድነት ከፍ ከፍ ለማድረግ ጊዜ መስጠት ይገባል።
6. በትምህርቱ የተማሩትን ነገር በተግባር ለመተርጎም እንዲችሉ መጸለይ ይገባቸዋል።
7. ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች፥ ለወንጌላውያንና ለሌሎች ቤተ ክርስቲያናት መጸለይ አስፈላጊ ነው።
8. እርስ በርስ መረዳዳትና አንዱ ለአንዱ መጸለይ ተገቢ ነው።

## ጥያቄዎች

1. ክርስቲያን ሴቶች ለኅብረተሰቡም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ?
2. አዎን ብለን የምንመልስ ከሆነ ምን ያህል ዕድል ሰጥተናቸዋል?
3. የሴቶች ስብሰባ ዋና ዓላማ ምንድን ነው?
4. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ከተጠቀመባቸው ሴቶች መካከል አንድ ምሳሌ መጥቀስ ትችላለህ?

# ክፍል ሦስት

# ልጆችን የማስተማር ዘዴ

## መግቢያ

ልጆችን ማስተማር የማን ኃላፊነት ነው?

ሀ. <u>የወላጆች</u>

በ2ኛ ጢሞ. 3፡15 ውስጥ ጢሞቴዎስ ከልጅነቱ ጀምሮ የጌታን ቃል ያውቅ እንደነበር እንረዳለን። 2ኛ ጢሞ. 1፡15 ደግሞ እናቱና አያቱ እግዚአብሔርን የሚፈሩ የእምነት ሰዎች እንደነበሩ ይነግረናል። ስለዚህ ጢሞቴዎስን እነርሱ እንዳስተማሩት አጠራጣሪ አይደለም። ኤፌ. 6፡4 አባቶች ልጆቻችሁን አስተምሩ ይላል። ይህንንም ስናደርግ ያለ ጥበብ እንዳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ርዳታና ምሪት ያስፈልገናል (1ኛ ቆሮ. 2፡4፥ 2ኛ ቆሮ. 3፡6)።

የሳሙኤልና የሙሴ ወላጆች ለልጆቻቸው እንዴት እንደተጠነቀቁላቸው ለማወቅ ታሪካቸውን የሚያቀርቡትን የብሉይ ኪዳን ክፍሎች አንብቡ። ቃሉን ለልጆቻችሁ አስተምሩ፥ ዘዳ. 6፡4-9፤ 11፡8-21። ልጆቻችሁ የሚጠይቁአችሁን ጥያቄዎች ለመመለስ ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ (ዘጸ. 12፡26፥ ኢያ. 6፡6-7)።

ለ. <u>የቤተ ክርስቲያን</u>

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶንና ለፊልጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክት ልጆችን ከቅዱሳን ጋር አንድ አድርጐ በመቁጠር ጠቅሶአቸዋል (ኤፌ. 6፡1፥ ቈላ. 3፡20)። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ልጆቻቸውን የጌታን ቃል ማስተማር አለባቸው። ከዚያም ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው እንዲቀበሉት መምራት ግዴታቸው ነው (1ኛ ጢሞ. 3፡4-5፤ 12፥ ቲቶ 1፡6)።

ሐ. <u>የእያንዳንዱ አማኝ</u>

ማንኛውም አማኝ ልጆቹን ለማስተማር ዝግጁ መሆን አለበት (ማቴ. 18፡1-14)። በማቴ. 18፡6 ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት ልጆች እንዴት ሊሰናከሉ ይችላሉ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ የተሳሳተ ትምህርት ከማስተማር ወይም ትክክለኛውን ትምህርት ካለማስተማር የተነሣ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕፃናትን እንዳስተማረ በማቴ. 18፡6፤ 13፤14 ውስጥ በግልጽ ተጠቅሷል። ልጆች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ሊቀበሉትና ሊያዩት ይችላሉ።

ሕፃናትን ፈልገን ወደ እርሱ እንድናመጣቸው የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር ይህንን ኃላፊነታችንን እንድንፈጽም ይፈልጋል (ማቴ. 19፡13-14)።

## ተጨማሪ ማመሳከሪያ ጥቅሶች

የሐ. 21:15-17:- ጴጥሮስ ጠቦቶችንና ግልገሎችን ጭምር እንዲመገብ ተነግሮታል።

የሐዋ. 20:8:- ለጠቅላላው መንጋ ተጠንቀቁ።

ኢሳ. 40:11:- ክርስቶስ ለግልገሎችና ለሚያጠቡት እኩል ይጠነቀቃል።

ሕዝ. 34:4-6:- ተግባራቸውን በትክክል ለማይፈጽሙ እረኞች የተሰጠ ከባድ ማስጠንቀቂያ አለ።

ሕዝ. 34:9-10:- ተግባራቸውን በዘነጉ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚመጣ ይናገራል።

1ኛ ቆሮ. 15:58 :- አገልግሎታችንን በታማኝነት እንድንቀጥል ያደፋፍረናል።

## ምክር ለመምህራን

1. "ለሰንበት ትምህርት ተማሪዎች የመምህሩ መመሪያ" የተባለውን መጽሐፍ ከዚህ ጋር አጣምረው መጠቀም አለባቸው። እያንዳንዱ ተማሪ ይህ መመሪያ መጽሐፍ ሊኖረው ይገባል።
2. እንዲሁም እያንዳንዱ መምህር ከመመሪያው ጋር በተጨማሪ "ጥናት በዘዴ" የተባለው መጽሐፍ ሊኖረው ይገባል።

## ጥያቄዎች

1. ልጆችን ማስተማር የማን ኃላፊነት ነው?
2. ልጆችን ስለ እግዚአብሔር በልጅነታቸው ማስተማር ያለብን ለምንድን ነው?
3. ልጆች ከእግዚአብሔር ቃል ሌላ መልካም ምሳሌነትን የሚማሩት ከማን ነው?
4. በልጆቻችን ፊት ምን ዓይነት ሰዎች ሆነን መታየት አለብን?

## አጠቃላይ መደምደሚያ

### ተማሪዎች ራሳቸውን መጠየቅ የሚገባቸው ጥያቄዎች

1. የአንድ አስተማሪ አቋም በተማሪዎች ፊት ምን ዓይነት መሆን አለበት?
2. መምህሩ በሚያስተምርበት ጊዜ አቋቋሙ እንዴት ነበር?
3. ትምህርቱን ሲያስተምር የአነጋገር ዘይቤው ምን ዓይነት ነበር?
4. መምህሩ ሲያስተምር ዓላማውን እስከ መጨረሻው ጠብቋል?
5. በሚያስተምርበት ወቅትስ ተማሪዎቹን በትምህርቱ ላይ የተመረኮዘ ጥያቄ ጠይቋል?
6. በሚያስተምረው ትምህርት ውስጥ የተማሪዎቹን አሳብ የሚሰበስብ መግቢያ ተጠቅሟል?
7. መምህሩ ለዕለቱ ትምህርት በቂ ዝግጅት አድርጓል?

8. በትምህርቱ ፍሬ ነገሮችን ለተማሪዎቹ ለማሳወቅ ሞክሮአል?
9. በትምህርቱ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ምሳሌዎችን ተጠቅሞአል?
10. ጥያቄዎችን በትምህርቱ መካከል ጣልቃ በማስገባት ተማሪዎችን ይጠይቃል?
11. ትምህርቱን በጸሎት ጀምሮ በጸሎት ይፈጽማል?

## የክፍል አንድ ጥያቄዎች መልሶች

1. ከኢየሱስ የማስተማር ዘዴ የሚከተሉትን መማር እንችላለን።
   - ከእግዚአብሔር የሆነውን ማስተማርን፤
   - እንደምናስተምረው ቃል መኖርን፤
   - የሚያሳስቱትን መገሠጽን
   - በመጀመሪያ የሰዎችን አሳብ መሳብን ወይም ማግኘትን፤
   - የውይይት ዘዴን መጠቀምን፤
   - ትምህርቱን በሌሎች ሰዎች ጥያቄዎች ላይ መገንባትን፤
   - በድፍረት መናገርን፤
   - ከቤተሰብ አካባቢ፥ ከግብርና አካባቢ፥ ከመሥሪያ ቤት አካባቢ፥ ከፖለቲካ አካባቢ፥ ከግል ልምምድ/ በመጠኑ/ በጊዜው ካለው ሁኔታ፥ ከተፈጥሮ፥ ከሌሎች የሕይወት ታሪክ፥ ከስብከት፥ ወዘተ... ምሳሌዎችን በመጠቀም ከቀላል ወደ ከባድ የሚለውን የማስተማር ዘዴ መጠቀምን፤
   - የሰዎችን ችግር አውቆ መፍትሔውን መናገርን፥
   - ካስተማርን በኋላ ተማሪዎቻችን በተግባር እንዲያውሉት ማድረግን ወዘተ....መማር እንችላለን።
2. የምናስተምረው ትምህርት ከሕይወታችን ጋር መመሳሰል ያለበት:-
   - በክርስቶስ አርአያነት በመኖር ለምናስተምራቸው ምሳሌ ለመሆን፤
   - እውነተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት ፍጹም የሆነ ዝግጅትና ሕይወትንም ጭምር ስለሚጠይቅ፤
   - ለእግዚአብሔር ፍጹምና ንጹህ የሆነ አገልግሎትን ለመስጠት፤
   - በጸሎትና ቃሉን በማንበብ የተገነባ ሕይወት ከሌለን ልፋታችን ፍሬያማ መሆን ስለማይችል፥ ወዘተ. ..።
3. ትምህርት ስናስተምር ሰዎች ከሚያውቁት ነገር ጀምረን ወደማያውቁት መሸጋገር ያለብን:-
   - አሳባቸውን ለመሰብሰብና ለመማረክ፤
   - ፍላጐት እንዲያድርባቸውና የሚሰጠውም ትምህርት እንዲገባቸው ወዘተ...ለማድረግ ነው።
4. ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የምንችለው:-
   - ደኅንነት ምን ማለት እንደሆነ በማስረዳት፤

- ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን እንዲያውቁ በማድረግ፤
- እግዚአብሔር ከዘላለም ፍርድ የምናመልጥበትንና አስደናቂ ፍቅሩን የምንቀበልበትን መንገድ ማዘጋጀቱን በማሳወቅ፥
- ሰዎቹ የደኅንነትን መንገድ እንዴት እንደሚቀበሉ በማሳየት።

# የክፍል ሁለት ጥያቄዎች መልሶች

1. አዎን።
2. አብዛኞቻችን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተፈቀደው ለወንድ፥ ለልጆች፥ ለሰባኪዎች፥ ለአባት፥ ለወንጌላውያን፥ ለመጋቢዎች፥ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ለመሳሰሉት እየመሰለን ልንሰጣቸው የሚገባውን ዕድል አልሰጠናቸውም።
3. የሴቶች ስብሰባ ዓላማ:-
   - አምልኮ
   - ኅብረት
   - ምስክርነትና
   - አገልግሎት ናቸው።
4. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ከተጠቀመባቸው ሴቶች መካከል ጵርስቅላ እንደ ምሳሌ የምትጠቀስ ናት።

# የክፍል ሦስት ጥያቄዎች መልሶች

1. ልጆችን ማስተማር:-
   - የወላጆች
   - የቤተ ክርስቲያንና
   - የእያንዳንዱ አማኝ ኃላፊነት ነው።
2. ልጆችን በልጅነታቸው ስለ እግዚአብሔር ማስተማር ያለብን:-
   - የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለሆነ (ኤፌ. 6:4፥ ዘዳ. 6:7)
   - ሕፃናትን ፈልገን ወደ እርሱ እንድናመጣቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ (ማቴ. 19:13-14)።
   - እንደ አካላቸው እድገት በመንፈሳዊ እድገታቸውም ከልጅነታቸው ጀምሮ እንዲዳብሩና እንዲበለጽጉ በእድሜያቸው ለረጅም ጊዜ እግዚአብሔርን ማገልገል እንዲችሉና ወዘተ ...ነው።
3. በቁጥር አንድ ውስጥ ከተጠቀሱት ነው።
4. በልጆቻችን ፊት:-
   - እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችንና በፍጹም አሳባችን በመውደድ ሰውነታችንን እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕያው መሥዋዕት አድርገን በማቅረብ አገልግሎታችንን በታማኝነት የምንወጣ፤
   - ልጆቻችንንና ሌሎችን የምናፈቅር፥ የእግዚአብሔርንም ቃል የምናስተምር ወዘተ.. .ሆነን መታየት አለብን።

====================//====================